የሰላም ሚኒስቴር

የ2013 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት ሪፖርት

ሚያዚያ/2014

አዲስ አበባ

የሰላም ሚኒስቴር
የ2013 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት

የሰላም ሚኒስቴር የተመደበለትን የመደበኛና ካፒታል በጀት በፋይናንስ አዋጅ፤ ደንብ እና በተከታታይ በወጡ መመሪያዎች መሠረት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን እንዲሁም ሂሳቡ በመንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት መያዙንና የመንግሥት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ ከዚህ ሪፖርት ጋር የተያያዙትን የ2013 በጀት ዓመት የሂሳብ ሪፖርቶች እና ማስታወሻዎች ኦዲት አድርገናል።

የሂሳብ ሪፖርቶቹን የማዘጋጀት የሰላም ሚንስቴር ሥራ አመራር ሲሆን፤ የሂሳብ ሪፖርቶቹን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ አስተያየት መስጠት ደግሞ የዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው ።

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ዓለምአቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን መሠረት በማድረግና የዋና ኦዲተርን የኦዲት ሥልት በመከተል ነው። እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ አጥጋቢ የሆነ ማረጋገጫ (የኦዲት አስተያየት) ለመስጠት ያስችለናል።

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት የሰላም ሚንስቴር ያቀረባቸው የሂሳብ ሪፖርቶች፤ መዛግብት ደጋፊ ማስረጃዎች እንዲሁም በሚንስቴር መ/ቤቱ ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው ።

ኦዲቱ የተከናወነው የዓመቱን የሂሳብ እቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው።

የሚከተሉት የሚንስቴር መ/ቤቱ የሂሳብ ሪፖርቶች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል።

- የገቢ /የዕርዳታ/የብድር ሂሳብ ሪፖርት፤
- የመደበኛና የካፒታል ወጪ ሂሳብ ሪፖርት፤
- የዝውውር ሂሳብ ሪፖርት፤
- የተሰብሳቢ ሂሳብ ሪፖርት
- የተከፋይ ሂሳብ ሪፖርት
- የሂሳብ ማመዛዘኛ ሪፖርት

የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው በአዋጅ በተፈቀደው በጀት እና በመንግስት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት በትክክል የተዘጋጁ እና የተሰበሰበው ገቢ፣ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ፣ ደንብና መመሪያ የጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

ወጪ፤

1. የፌደራል መንግስት መ/ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል 2 ተራ ቁጥር 8(2/ለ) የወጪ ሂሳብ ወጪ ከመደረጉ በፊት ስለወጪው የተሟላ ማስረጃ ማቅረብና ስልጣን ባለው አካል መፈቀድ አለበት ይላል። በዚሁ መሰረት በተቋሙ ስም የስልክ መስመሮች ለተሰጠ አገልግሎት ብቻ ክፍያ የተፈጸመ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ የተቋሙ የስልክ ቁጥሮች ዝርዝር ውስጥ ባልተካተቱ የስልክ መስመሮች በድምሩ ብር 61,521.33 የስልክ ፍጆታ ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል። በዚህም የበጀት ዓመቱ የወጪ ሂሳብ ከፍ እንዲል አድርጓል።
2. የፌዴራል መንግሥት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ዓ.ም. በክፍል ሁለት አንቀፅ 6 ተራ ቁጥር 4 ላይ የመንግስት መስሪያ ቤቶች በበጀት አደረጃጀት ሥርዓት መሠረት የተፈቀደላቸው በጀትና የወጣውን ወጪ በሚያሳይ መልኩ ተለይቶ በተሰጠ የበጀት መለያ መደብ ተጠቅመው የሂሳብ እንቅስቃሴያቸውን መመዝገብ እንዳለባቸው ይገልጻል:: ይሁን እንጂ ለችግኝ መግዣ የተከፈለ ብር 103,850.00 በሂሳብ መደብ 6221 (2211110) በወጪ መመዝገብ ሲገባው በሂሳብ መደብ 6217 (2211107) ተመዝግቦ ተገኝቷል።

በጀት፤

3. በፌዴራል መንግስት የገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት 6/2 ላይ የበጀት ዝውውር ወይም ተጨማሪ በጀት ካልተፈቀደ በስተቀር ለአንድ የመንግስት መ/ቤት በሂሳብ መደብ ተለይቶ ከተፈቀደው በጀት በላይ ወጪ መፈጸም እንደማይቻል ይገልጻል። ይሁን እንጂ በሂሳብ መደብ 6241(2231107) ብር

5,068,066.57 እንዲሁም በሂሳብ መደብ 6258 (2241108) ብር 119,119.01 በድምሩ ብር **5,187,185.58** ለመደበኛ በጀት ከተፈቀደው በላይ ወጪ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ከላይ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 4 በተገለጹት ጉልህና መሠረታዊ ልዩነቶች የተነሳ በእኛ አስተያየት የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሂሳብ ሪፖርቶች ሰኔ 30 ቀን 2013 ዓ.ም. የተመለከተውን የፋይናንስ አቋም እና የበጀት ዓመቱን የሥራ እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እንዲሁም የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት በአጥጋቢ ሁኔታ አያሳዩም፡፡

ትኩረት የሚያሻቸው ጉዳዮች፤

ገቢ፤

1. በሂሳብ መደብ 1451199/1489 የተያዘ ከልዩ ልዩ ገቢ የተሰበሰበ በድምሩ ብር 15,620.00 በገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኙ ላይ ፣ የገቢው ምክንያት ባለመገለጹ የገቢውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

የወጪ ሂሳብ፤

2. ሰኔ/2002 በወጣው የፌዴራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ክፍል 4 አንቀጽ 15.2-15.4 መሠረት በአዋጁና በመመሪያው በተፈቀደው ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር የመንግስት መ/ቤቶች ማናቸውንም ግዥ በግልፅ የጨረታ ዘዴ መፈጸም እንዳለባቸው ይገልጻል፡፡ ይሁን እንጂ በተለያዩ ቀናትና የወጪ ማስመስከሪያዎች በድምሩ ብር 52,742,812.67 ያለወድድር የተለያዩ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ግዥ ለተከናወነበት የተከፈለ ሲሆን፤ አቅራቢዎችን በማወዳደር እንዲገዛ መደረግ ሲገባው በቀጥታ ግዥ ተፈፅሞ ተገኝቷል፡፡
3. ታህሳስ 2008 የግዥ መመሪያን አንዳንድ አንቀጾች ለማሻሻል በወጣው መመሪያ ከብር 150,000.00 በላይ የአገልግሎት ግዥ እንዲሁም ከብር 200,000.00 በላይ ለዕቃ ግዥ ጨረታ መውጣት እንዳለበት ይገልጻል፡፡ ይሁን እንጂ ሚኒስቴር

መ/ቤቱ በተለያየ ቀንና የወጪ ማስመስከሪያ በድምሩ በብር 6,089,671.24 ከመመሪያ ውጭ በዋጋ ማወዳደሪያ የአገልግሎት ግዥ ፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

4. የፌደራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 አንቀጽ 14/1 እና 2 የመደበኛና የካፒታል የሥራ መስኬጃ ወጪዎች ሲፈጸሙ፤ ወጪው ለሚደረግበት ተግባር በበጀት ዓመቱ የተያዘ ወይም ወጪውን ለመሸፈን ቀሪ በጀት መኖሩንና ወጪው በመስሪያ ቤቱ ዕቅድ ውስጥ የተያዘና በጥሬ ገንዘብ ፍላጎት እቅድ ላይ የተካተተ መሆኑ ሳይረጋገጥ ክፍያ መፈጸም እንደማይገባ ይገልጻል፡፡ ይሁን እንጂ የ2012 በጀት ዓመት፤ የሚያዝያ፤የግንቦት እና የሰኔ ወር 2012 የስልክ አገልግሎት ክፍያ በሂሳብ መደብ 2241108/6258 በዕቅድ ሳይያዝና በጀት ሳይጠየቅ ለ2013 በጀት ዓመት ከተፈቀደው በጀት ለዘመን ቴሌኮም ኃ/የተ/የግ ማህበር በድምሩ ብር 719,904.59 በጀት ዓመቱን ሳይጠብቅ ክፍያ ተፈጽሞና በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

5. መ/ቤቱ የካቲት 2012 ባወጣው የስልክ፣ሲዲኤምኤ፣የመስተንግዶ እና አላቂ እቃዎች አጠቃቀም መመሪያ መሰረት ክፍያዎች የሚፈፀሙ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በመ/ቤቱ የሰው ሀይል ዝርዝር ውስጥ ላልተካተቱ እና የመ/ቤቱ ሰራተኞች ያልሆኑ ግለሰቦች ለተጠቀሙበት የስልክ አገልግሎት ብር 55,176.38 ክፍያ ተፈፅሞ ተገኝቷል፡፡

6. የፌዴራል መንግሥት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ዓ.ም. በክፍል ሁለት አንቀፅ 6 ተራ ቁጥር 4 ላይ የመንግስት መስሪያ ቤቶች በበጀት አደረጃጀት ሥርዓት መሠረት የተፈቀደላቸው በጀትና የወጣውን ወጪ በሚያሳይ መልኩ ተለይቶ በተሰጠ የበጀት መለያ መደብ ተጠቅመው የሂሳብ እንቅስቃሴያቸውን መመዝገብ እንዳለባቸው ይገልጻል:: ይሁን እንጂ በመ/ቤቱ በተለያዩ የወጪ ማስመስከሪያዎች የተከፈሉ በድምሩ ብር 7,048,052.89 በተገቢው የሂሳብ መደብ ሳይመዘገቡ ተገኝተዋል፡፡

7. በፌዴራል መንግስት የግዥ አፈፃፀም መመሪያ መሰረት በውስን ጨረታ የሚፈጸም ግዥ ላይ በጨረታው ተሳታፊ ሊሆን የሚችሉ አቅራቢዎች ቁጥር በርካታ ቢሆኑም በመመሪያው በተቀመጠው ገደብ ውስጥ ከሆነ ከአቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ መካከል ፍትሃዊ በሆነ ምርጫ ቢያንስ አምስት እጩ ተወዳዳሪዎችን መምረጥ እንደሚቻል ይገልጻል፡፡ ይሁን እንጂ መ/ቤቱ ለመስክ የመኪና ኪራይ ከጥረት የመኪና

ማከራየትና ፕሮሞሽን በብር 704,000.00 እንዲሁም ለየአይሲቲ እና ለሌሎች እቃዎች ግዥ ብር 1,459,810.00 ከታቦር ቴክኖሎጂ ሶሉሺንስ ኃላ/የተ የግ.ማህበር በድምሩ ብር 2,163,810.00 በውስን ጨረታ ግዥ የተፈጸመ ሲሆን፤ ከአቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ ፍትሃዊ በሆነ መንገድ ተወዳዳሪዎች ስለመጋበዛቸው የሚያሳይ ማስረጃ ባለመቅረቡ የግዥውን ፍትሃዊነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

ተሰብሳቢ ሂሳብ፤

8. በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 32፣የፌደራል መንግሥት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 እንዲሁም በፌዴራል የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 መሰረት ቅድሚያ ክፍያዎች በወቅቱ እንዲወራረዱ ያዛል፡፡ ይሁን እንጂ፤
   - በ4210 (5217109) የሂሳብ መደብ ብር 70,819,888.58 1 ዓመት የቆየ፤
   - በ4253 (5217205) የሂሳብ መደብ ብር 168,095,583.46 1 ዓመት የቆየ፤

   እንዲሁም ብር 39,950,196.01 ከአምስት አመት በላይ የቆየ፤

በድምሩ ብር 278,865,668.05 በድንቡና በመመሪያው መሰረት በወቅቱ ሳይወራረድ ተገኝቷል፡፡

የተከፋይ ሂሳብ፤

9. በፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 8 ንኡስ አንቀጽ 5 በተመለከተው መሰረት ተከፋይ ሂሳቦችን ለመከታተል ተገቢው የቁጥጥር ስርዓት መዘርጋቱንና ሂሳቡም በወቅቱ መከፈሉን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

   በተለያዩ የሂሳብ መደቦች በተከፋይ የተያዘ በድምሩ ብር 123,715,072.74 በወቅቱ ለባለመብቱ ሳይከፈል ተገኝቷል፡፡

ስራ ላይ ያልዋለ በጀት፤

10. የመደበኛ በጀት ብር 434,075,023.35 እንዲሁም የካፒታል በጀት ብር 286,479,898.33 በድምሩ ብር 720,554,921.68 ስራ ላይ ያልዋለ በጀት ተገኝቷል፡፡

ሌሎች ጉዳዮች

11. **ንብረት፤**

- የንብረት መጋዘን ውስጥ ቋሚና አላቂ እቃዎች፤ የሚወገዱና የማይወገዱ በአንድ የንብረት መጋዘን ውስጥ ተቀላቅለው ተገኝተዋል።
- መወገድ የሚገባቸው ወንበሮች፤ ጠረጴዛ፤ ፋይልካቢኔት እና ኮፊ ቴብል ኮምፒውተር የመሳሰሉት ሳይወገዱ ለቁጥጥር በማይመች መልኩ ተከማችተው ተገኝተዋል፤
- ብዛት ያላቸው የመኪና ጎማዎች፤ የመኪና መለዋወጫ ዕቃዎች፤ ፈርኒቸሮች (የኃፊዎች፤ የባለሙያ እና የእንግዳ ወንበሮች)፤ ጠረጴዛዎች፤ጋቢ እና የደንብ ልብሶች እቃ ግምጃ ቤት ውስጥ ለቁጥጥር በማይመች መልኩ የተቀመጡ መሆኑ ተረጋግጧል።
- በሚ/ር መ/ቤቱ ስም የባለቤትነት መታወቂያ ያልተዘጋጀላቸው በተለያየ መ/ቤት ስም የተመዘገቡ 85 ተሽከርካሪዎች መኖራቸው፣
- የሰሌዳ ቁጥር 4-21970 የጠፋ ተሽከርካሪ፣ 4-13113፤4-03397 የወደሙ በአጠቃላይ በበላይ አመራሩ ውሳኔ ሳይሰጣቸው መገኘታቸው፣
- ይወገዳሉ ተብሎ ወደ ሌላ መ/ቤት የተላለፉ ስምንት ተሽከርካሪዎች የመጨረሻ ውሳኔ አለመታወቁ፤
- የሰሌዳ ቁጥር UN1609፤ 4-17076፤ 4-22452 እና 4-08387 የባለቤትነት መታወቂያ (ሊብሬ) የሌላቸው ተሽከረካሪዎች መገኘታቸው፣

12. **ክትትል ኦዲት፤**

የ2012 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶች

- በመመሪያ ከተቀመጠው የስልክ ክፍያ ገደብ በላይ የተከፈለ ብር 317,750.24 ከሚመለከታቸው ግለሰቦች ተመላሽ እንዲደረግ አስተያየት ቢሰጥም ገንዘቡ ያልተመለሰ መሆኑ፤
- ከሚመለከተው አካል ፈቃድ ሳይገኝ የተፈጸሙ የትርፍ ሰዓት ክፍያ ብር 29,321.613 ተመላሽ እንዲደረግ እንዲሁም ማስረጃ ያልቀረበላቸው ማስረጃ እንዲቀርብ አስተያየት ቢሰጥም ገንዘቡ ያልተመለሰና ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ ታውቋል።

የ2011 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶች

- ከቤት አበል ተቀናሽ ያልተደረገ ግብር ብር 20,700.00 ከግለሰቦቹ ላይ ተሰብስቦ ለመንግስት ገቢ እንዲደረግ አስተያየት ቢሰጥም ያልተሰበሰበ መሆኑ፤
- በብልጫ የተከፈለ ውሎ አበል በድምሩ ብር 410,024.00 ከግለሰቦቹ ተመላሽ እንዲደረግ አስተያየት ቢሰጥም ተመላሽ አለመደረጉ፤
- በመ/ቤቱ ስም ላልተመዘገበ የሞባይል ስልክ ወጪ የሆነ የአገልግሎት ክፍያ በድምሩ ብር 5,274.17 ተመላሽ እንዲደረግ አስተያየት ቢሰጥም ተመላሽ አለመደረጉ፤
- ለኦዲት ያልቀረቡ ሰነዶች ብር 47,724,348.01 ማስረጃቸው እንዲቀርብ በኦዲት አስተያየት ቢሰጥም ማስረጃ አለመቅረቡ፤

የ2010 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶች

- ሰራተኞች ላልሰሩባቸው ቀናት በድምሩ ብር 26,423.80 አለአግባብ ተከፍሎ በመገኘቱ ከሚመለከታቸው ግለሰቦች ተመላሽ እንዲደረግ አስተያየት ቢሰጥም ገቢ አለመደረጉን፤
- ከንብረት ክፍል ወጪ ሆነው አገልግሎት ላይ ያልዋሉ የመኪና ጎማዎች ግዥ ብር 96,600.0 አገልግሎት ላይ ባለማዋላቸው የሚመለከታቸው ሃላፊዎች ተጠያቂ ስለመሆናቸው ማስረጃ አልቀረበም፡፡
- ንብረቶች ገቢ ሳይደረጉ የተፈፀመ ክፍያ ብር 858,731.08 በሚመለከት ንብረቱ ለመ/ቤቱ አገልግሎት ለመዋሉ ማረጋገጫ እንዲቀርብ ወይም ገንዘቡ ከሚመለከተው አካል ተመላሽ እንዲሆን አስተያየት ቢሰጥም ተመላሽ አለመደረጉ፤
- አለአግባብ ለውሎ አበል የተከፈለ በድምሩ ብር 66,934.40 ከሚመለከታቸው ሠራተኞች እና የስልጠና ተሳታፊዎች ተመላሽ እንዲደረግ አስተያየት ቢሰጥም ተመላሽ አለመደረጉ፤
- ለአየር ትኬት በድጋሚ የተከፈለ ብር 67,321.00 እና የተሟላ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገበ ብር 1,781,598.65 በመመሪያው መሠረት ለወጪው ተገቢው ማስረጃ ሊቀርብ ወይም ገንዘቡ ከሚመለከታቸው ተመላሽ ሊደረግ እንደሚገባ አስተያየት ቢሰጥም ገንዘቡ ገቢ አለመደረጉን ማስረጃዎችም አለመቅረባቸው ታውቋል፡፡

የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶች

- የነዳጅ ግዥና ለሠልጣኞች የትራንስፖርት አበል በድምሩ ብር 89,229.15 የክፍያ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ ሂሳብ በመመዝገቡ ህጋዊ ማስረጃ እንዲቀርብለት አስተያየት ቢሰጥም ማስረጃ አለመቅረቡ ፡፡
- በድምሩ ብር 157,475.00 ያለአግባብ የተከፈለው ገንዘብ ተመላሽ እንዲደረግ ወይም ክፍያውን ከፈቀደው ኃላፊ ተመላሽ እንዲያደርግ አስተያየት ቢሰጥም እርምጃ አለመወሰዱ፤
- መ/ቤቱ የአገልግሎትና የዕቃ ግዥ ፈጽሞ በተለያዩ 9 የወጪ ቫውቸሮች የተሟላ ደጋፊ ማስረጃ ሳይኖር በድምሩ ብር 284,588.36 ክፍያ በመፈጸሙ ቀሪ ማስረጃዎች እንዲቀርቡ አስተያየት ቢሰጥም እርምጃ አለመወሰዱ፤
- ከግንቦት/2009 ዓ.ም - ሰኔ 2009 ዓ.ም ወጪ የተደረገባቸው የክፍያ ሰነዶች ማስረጃው ባለመቅረቡ የሂሳቡን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ባለመቻሉ ማስረጃዎቹ ተፈልገው ሊቀርቡ እንደሚገባና በውስጥ ኦዲት በኩልም ሰነዶቹ ተጣርተው ሪፖርት ሊቀርብ እንደሚገባ አስተያየት ቢሰጥም እርምጃ ያለመወሰዱ፤
- ከመ/ቤቱ ለተሰናበቱ ሰራተኛ ለወ/ሮ እየሩሳሌም አስፋው ብር 2,691.63 ፣አቶ ጎይቶመ ጽጋብ ብር 5,478.80 ፣ ወ/ሮ ቃልኪዳነ ካሳ ብር 2875.17፣ ወ/ሮ አመለወርቅ ጉዲሳ ብር 1,846.88፣ አቶ ታጁ ሙክታር ብር 4,791.67፣ ሰለሞን ያይንሸት ብር 2,779.78 እና ብርሀኑ ሀይሉ ብር 1,663.50 በድምሩ ብር **22,127.43** መ/ቤቱ ከለቀቁ በኂላ በተለያየ ጊዜ ደሞዝ ተከፍሏቸው ተገኝቷል፡፡

ከሰላምታ ጋር

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

የሰላም ሚኒስቴር የ2013 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት

የሥራ አመራር ሪፖርት

መግቢያ

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን መሰረት የሰላም ሚኒስቴር የ2013 በጀት ዓመት ሂሳብ ላይ የኦዲት አስተያየታችንን ለመስጠት ያስችለን ዘንድ ኦዲት አድርገናል፡፡

የሪፓርቱ ዓላማ

የዚህ የሥራ አመራር ሪፖርት ዓላማ በኦዲታችን ወቅት የተገኙትን የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች እና ሌሎች ግድፈቶች የሰላም ሚኒስቴር የበላይ አመራር አካላት እንዲያውቁትና ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ እንዲወስዱ ለማድረግ ነው ፡፡

የኦዲቱ ወሰንና ኃላፊነት

ኦዲቱ የተከናወነው ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን መሠረት በማድረግ እና የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን የኦዲት ሥልት በመከተል ነው፡፡እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት ሚ/ር መ/ቤቱ ባዘጋጃቸው የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ አጥጋቢ የሆነ ማረጋገጫ /የኦዲት አስተያየት /ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ኦዲታችን የሚያካትተው፤

- በሂሣብ ሪፖርቶቹ ላይ የሠፈሩት አሀዞችና ሪፖርቶቹን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና መመርመር፤
- የሥራ አመራሩ የሂሣብ ሪፖርቶቹን ሲያዘጋጅ ያደረጋቸውን ጉልህ ግምቶች እና ውሣኔዎችን መመዘን፤
- የሚንስቴር መ/ቤቱ የሂሣብ አያያዝ በፌዴራል መንግስት የሂሳብ አያያዝ ማዕቀፍ መሰረት መሆኑን ከዓመት ዓመት ሳይቀያየር በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የሂሣብ ሪፖርቶቹ አግባብነት ያላቸውን አዋጆች፣ደንቦችና መመሪያዎች በመከተል የተዘጋጁ መሆኑን መመርመርን ይይዛል፡፡

የሂሣብ ሪፖርቶቹ ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የጸዱ ለመሆናቸው በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል፡፡የኦዲት አስተያየት ላይ ለመድረስ በሂሣብ ሪፖርቶቹ ላይ ያለውን የመረጃ አቀራረብ አጠቃላይ ብቃት ገምግመናል፡፡

ይሁን እንጂ በዚህ ሪፖርት ላይ ከተመለከቱት የአሠራርም ሆነ የሂሣብ አያያዝ ድክመቶች በተጨማሪ ሌሎች ድክመቶች ወይም ስህተቶች ሊኖሩ ስለሚችሉ የሂሣብ ሪፖርቶቹን ለማዘጋጀት የተዘረጉትን የውስጥ ቁጥጥርና ሌሎች ድክመቶችን ሙሉ በሙሉ ሊያሣይ አይችልም፡፡

የሂሣብ ሪፖርቶቹን የማዘጋጀት ኃላፊነት የሚኒስቴር መ/ቤቱ ሥራ አመራር ሲሆን፣የሂሣብ ሪፖርቶቹን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው፡፡

የሚ/ር መ/ቤቱ የ2013 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሣቦች ከዚህ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

1.የገቢ ሂሳብ፤

1.1 ግኝት፡- የገቢውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ ብር 15,620.00

በሚኒስቴር መ/ቤቱ የተሰበሰቡ የአገልግሎት እና የቅጣት ክፍያዎች የሃይማኖት ድርጅቶችና ማህበራት ምዝገባ አገልግሎት ክፍያ ተመን መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በሂሳብ መደብ 1451199/1489 (ከልዩ ልዩ ገቢ) በናሙና ከተመረጠው ውስጥ ጠቅላላ ድምር ብር 15,620.00 በገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኙ ላይ ፣ የገቢው ምክንያት ባለመገለጹ የገቢ አሰባሰቡ በመመሪያው መሰረት መሆኑን ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡ በባለፉት የኦዲት ሪፖርቶች እንደዚህ አይነት ግኝቶች ማስተካከያ እንዲደረግባቸው ቢገለጽም ማስተካከያ አልተደረገም ፡፡

ስጋት፤

- በተመኑ መሠረት ገቢዎች ላይሰበሰቡ ይችላሉ፡፡
- ፍትሀዊ የአገልግሎት አሰጣጥ ላይኖር ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

ከስራ ክፍሉ ተጽፎ በሚመጣልን መሰረት ነው ቢባልም ከዚህ በፊትም በኦዲት አስተያየቶች እንደተገለጸው የገቢ ደረሰኞች ላይ የገቢው ምክንያት በግልጽ ሊጻፍ ወይም የሚመለከተው የሥራ ክፍል የጻፈው የገቢ ማዘዣዎች ከገቢ ደረሰኞቹ ጋር በአባሪነት ሊያያዙ ይገባል ፡፡

የስራ አመራሩ ምላሽ፤

መ/ቤቱ በአዋጅ ከተሰጠው ተግባርና ኃላፊነቶች አንዱ የሃይማኖት ድርጅቶችና ማህበራት ምዝገባና ፈቃድ እድሳት ማድረግ፣ በፈቃድና እድሳት ዙሪያ የተለያዩ አገልግሎቶችን መስጠት

ሲሆን መ/ቤቱ ለሚሰጣቸው የተለያዩ አገልግሎቶች ተመጣጣኝ ክፍያ ለማስከፈል እንዲችል በፌዴራል መንግስት የዕቃና የአገልግሎት ክፍያ ተመን ተዘጋጅቶ በጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት በኩል እንዲጸድቅ ሐምሌ 16 ቀን 2004 በቁጥር መ70-2/1030/8 በተፃፈ ደብዳቤ የተላከ ሲሆን በተዘጋጀው የክፍያ ሰነድ ላይ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በሰጠው አስተያየት መሠረት የአገልግሎት ክፍያ ተመኑ በስራ ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡

ሆኖም የዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት ኦዲተሮች የሂሳብ ምርመራ በሚያደርጉበት ወቅት በገቢ አሰባሰቡ የገቢው ምክንያት አለመገለጹ እንደ ስጋት መቅረቡ ተገቢና የማስተካከያ ርምጃ መውሰድ የሚገባ መሆኑን የተገንዘብን ሲሆን

የተሰበሰበው ገንዘብ ብር 70,060 የገቢው ምክንያት ባለመገለፁ የገቢ አሰባሰቡ በመመሪያው መሰረት መሆኑን ማረጋገጥ አልተቻለም በሚል 26 የገቢ ደረሰኞች እንደማሳያ ተለየተው የቀረቡ ሲሆን ለአብነት ያህል

1ኛ. በቀን 27/07/2013 በደረሰኝ ቁጥር 537 ተመን ሳይወጣ የተሰበሰበ በሚል የቀረበ ብር 27,000፤

2ኛ. በቀን 27/07/2013 በደረሰኝ ቁጥር 536 ተመን ሳይወጣ የተሰበሰበ በሚል የቀረበ ብር 26,400

የቀረበዉን አስተያየት መነሻ በማድረግ የተጠቀሱትን የገቢ ደረሰኞች የከፋዮቹን የሀይማኖት ተቋማት ማህደር በመፈተሸ ማረጋገጥ እንደተቻለው በተራ ቁጥር አንድ እና ሁለት ከተገለጹት በድምሩ ብር 53,400 ብር የያዙትን ደረሰኞች የፈተሸን ሲሆን በሁለቱ ደረሰኞች ክፍያዉን የፈጸመው ናጂያ እስላማዊ ማህበር የሚባል የሀይማኖት ተቋም ሲሆን የክፍያዉ ምክንያት የስራ ክንዉን ሪፖርት በ135 ወር በማዘግየት ብር 27,000 ቅጣት እንተደከፈለና ይህንን ክፍያ ከመመሪያዉ አንፃር ስናስተያይ የሥራ ክንውን እና የኦዲት ሪፖርት በአንድ ወር ላዘገየ ብር 200 ቅጣት እንደሚከፍሉ በመመሪያዉ ስለተደነገገ በዚህ መሰረት 135 ወር *200ብር=ብር 27,000 ስለሚሆን በዚህ አግባብ የተከፈለ መሆኑን፡፡

በተራ ቁጥር ሁለት ላይ የተጠቀሰው እንዲሁ የናጂያ እስላማዊ ማህበር ሲሆን የክፍያዉ ምክንያት ፈቃዳቸዉን በ130 ወር በማዘግየት ብር 26,400 እንደከፈሉ የተረዳን ሲሆን ይህንን ክፍያ ከመመሪያዉ አንፃር ስናስተያይ ፈቃዳቸዉን ለ130 ወራት ሳያሳድሱ ለቀሩ 130 ወር *200ብር+መነሻ 400ብር =26,400 ቅጣት እንደሚከፍሉ ያዛል፡፡ ስለሆነም

ክፍያዉ የተከናወነው በመመሪያዉ መሰረት መሆኑን እናከተመኑ አንጻር ስህተት እንደሌለ ነገር ግን በገቢ ደረሰኞች ላይ የገቢውን ምክንያት አለመግለጽ በቀጣይ መታረም የሚኖርበት እንደሆነ ስለተረዳን በኦዲት ግኝትነት ባይመዘገብ እየጠየቅን ለማስረጃነት ያህል ከላይ የተጠቀሱትን ሁለት ደረሰኞች በአባሪነት አያይዘን አቅርበናል፡፡

የኦዲተሩ አስተያየት፤

ከብር 70,060.00 ግኝት ውስጥ በስራ አመራሩ ምላሽና ከመውጪያ ስብሰባ በኋላ በድምሩ ለብር 54,440 ማስረጃ የቀረበ ሲሆን ለቀሪው ብር 15,620.00 ማስረጃ አልቀረበም በመሆኑም በተሰጠው የኦዲት ማሻሻያ ሃሳብ መሰረት የገቢ ማዘዣዎች ከገቢ ደረሰኞቹ ጋር በአባሪነት ሊቀርቡ ይገባል፡፡

2. የወጪ ሂሳብ፤

2.1. ግኝት፤ በግልጽ ጨረታ መገዛት ሲገባው በቀጥታ ከአንድ አቅራቢ ለተፈፀመ ግዥ የተከፈለ ብር 52,742,812.67

ሰኔ/2002 በወጣው የፌዴራል መንግስት የግዥአፈጻጸም መመሪያ ክፍል 4 አንቀጽ 15.2-15.4 መሠረት በአዋጁና በመመሪያው በተፈቀደው ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር የመንግስት መ/ቤቶች ማናቸውንም ግዥ በግልፅ የጨረታ ዘዴ መፈጸም እንዳለባቸው፣ የመንግስት መ/ቤቶች ከግልፅ ጨረታ ውጭ በሌሎች የግዥ ዘዴዎች ግዥ መፈጸም የሚችሉት በአዋጁና በዚህ መመሪያ የተገለጹት ሁኔታዎች ሲሟሉ ብቻ እንደሆነ እንዲሁም ከግልጽ ጨረታ ውጭ በሌሎች የግዥ ዘዴዎች የሚጠቀም ማናቸውም የመንግሥት መ/ቤት በእነዚህ ዘዴዎች ለመጠቀም የመረጠበትን ምክንያትና ሁኔታዎች የሚገልጽ ሠነድ መያዝ እንዳለበት ይገልጻል፡፡ ይሁን እንጂ በተለያዩ ቀናትና የወጪ ማስመስከሪያዎች በድምሩ ብር 52,742,812.67 ያለወድድር የተለያዩ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ግዥ ለተከናወነበት የተከፈለ ሲሆን፤ አቅራቢዎችን በማወዳደር እንዲገዛ መደረግ ሲገባው በቀጥታ ግዥ ተፈፅሞ ተገኝቷል፡፡

ስጋት፤

- የተለያዩ አቅራቢዎችን በማወዳደር ሊገኝ በሚችለው የዋጋ ቅናሽ ጥቅም ሊያሳጣ ይችላል፡፡
- ፍታሃዊ ግዥ ላይከናወን ይችላል፡፡

- ከደንብና መመሪያ ውጭ ግዥ በመፈፀሙ መ/ቤቱ ለተጨማሪ ወጪ ሊዳረግ ይችላል፡፡

<u>የማሻሻያ ሀሳብ፤</u>

ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከተቋቋመበት አላማ አንጻር ግዥዎቹን አስቀድሞ ማቀድ የሚቻልና ቀድሞ ውድድር በማድረግ እና ከድርጅቶች ጋር ውል በመግባት ግዥውን ማስኬድ የሚቻል በመሆኑ ምላሹን አልተቀበልነውም፡፡ በመሆኑም ከመመሪያ ውጭ ለተፈፀሙ ግዥዎች ሚ/መቤቱ ግዥውን ከአንድ አቅራቢ የፈፀመበትን ምክንያት የሚገልፅ ማስረጃ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡ ለወደፊቱም በወጣው የግዥ አፈፃፀም መመሪያ መሰረት እንዲፈፅም ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡

<u>የስራ አመራሩ ምላሽ፤</u>

በኦዲት ማሻሻያ ሀሳብ ላይ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከተቋቋመበት አላማ አንጻር አሰቀድሞ ማቀድ የሚችልና ቀድሞ ውድድር በማድረግ እና ከድርጅቶች ጋር ውል በመግባት ግዥ ማስካሄድ የሚችል በመሆኑ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከመመሪያ ውጪ ለተፈፀሙ ግዥዎች ከአንድ አቅራቢ የፈፀመበትን ማስረጃ እንዲቀርብ በኦዲት ማሻሻያ ሃሳብ ላይ በተገለፀው መሰረት ተቋሙ ከተቋቋማበት አላማ አንፃር ሁሉንም ግዥዎች በእቅድ መምራት ተገቢ እንደሆነ የተሰጠውን አስተያየት በአውንታዊ ጎኑ በመቀበል በቀጣይ ለማረም ጥረት ይደረጋል፡፡ ሆኖም ተቋሙ ካለው የተለየ የስራ ባህሪይ አንጻር ሀገራዊ ፋይዳ ያላቸው አስቸኳይ የፀጥታ ስራዎች እና ከጠቅላይ ሚኒስትር ፅ/ቤት የሚታዘዙ አሰቸኳይ የስራ ትዕዛዞችና ከወቅታዊ ሁኔታ ጋር ተያይዞ የሚመጡ ስራዎች በመሆናቸው አስቀድሞ በእቅድ ከተያዙ ስራዎች ውጪ ደራሽ ስራዎች በብዛት አጋጥመውናል፡፡ ይህም ቢሆን በተቻለ መጠን ከመመሪያ ውጪ የተፈፀመ ሳይሆን የፌደራል የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 641/2001 አንቀፅ 51 ንኡስ አንቀፅ 5/2 በሚፈቅደው መሰረት በጣም አስቸኳይ በመሆኑ የተነሳ ከባድ ችግር የሚፈጥር እና በመስሪያ ቤቱ ስራ አፈፃፀም ላይ ጉዳት የሚያስከትል መሆኑ እየታየ በኤጀንሲውና በመ/ቤቱ የበላይ ሃላፊ በደብዳቤ ታዞ የግዥ አፈፃፀም መመሪያን ጠብቆ የተፈፀመ ግዥ ነው፡፡ በዚህም መሰረት ግዥውን ከአንድ አቅራቢ ሳይሆን በቀጥታ ግዥ የተፈጸመበትን ምክንያት የሚገልፅ በመ/ቤቱ የበላይ ሃላፊ የቀጥታ ግዥ ትእዛዝ የተሰጠበትን ደብዳቤ እና ምክንያቱን የሚገልፅ ማስረጃ አባሪ (3) ተያይዟል፡፡

የኦዲተሩ አስተያየት፤

የመ/ቤቱ ሃላፊ የቀጥታ ግዥው እንዲከናወን የወሰኑበት ምክንያት ከግዥ መመሪያው አንጻር አሳማኝ ሆኖ አላገኘነውም በመሆኑም በተሰጠው የኦዲት ማሻሻያ ሃሳብ መሰረት ለወደፊቱ የእርምት እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

2.2 ግኝት፤ በግልጽ ጨረታ መፈጸም ሲገባ በዋጋ ማቅረቢያ የተፈጸሙ ግዥዎች ብር 6,089,671.24፤

ታህሳስ 2008 የግዥ መመሪያን አንዳንድ አንቀጾች ለማሻሻል በወጣው መመሪያ ከብር 150,000.00 በላይ የአገልግሎት ግዥ እንዲሁም ከብር 200,000.00 በላይ ለዕቃ ግዥ ጨረታ መውጣት እንዳለበት ይገልጻል፡፡ በዚህም መሠረት መፈጸሙ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ ሚንስቴር መቤቱ በተለያየ ቀንና የወጪ ማስመስከሪያ በድምሩ በብር 6,089,671.24 ከመመሪያ ውጭ በዋጋ ማወዳደሪያ የአገልግሎትና ግዥ ፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

ስጋት፤

ፍትሐዊ የገበያ ውድድር እንዳይኖር ሊያደርግ ከመቻሉም በላይ መንግስት ከሌሎች አቅራቢዎች ሊያገኝ የሚችለውን ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ሊያሳጣ ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ፤

የመኪና ኪራይ አገልግሎት በውስን ጨረታ ግዥ እንደተፈጸመ ቢገለጽም በግዥ መመሪያው መሰረት በአቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ ከተመዘገቡት መካከል ፍትሃዊ በሆነ ምርጫ ቢያንስ አምስት ተወዳዳሪዎች ስለመመረጣቸው የሚያሳይ ማስረጃ ለኦዲት ስራ አልቀረበም፡፡ በመሆኑም ከአቅራቢ ዝርዝር ውስጥ ፍትሃዊ ምርጫ ስለመደረጉ የሚያሳይ ማስኛ ለኦዲት ስራው ሊቀርብ ይገባል፡፡

የመስተንግዶ አገልግሎትን በሚመለከት በተደጋጋሚ ጨራታ እንደወጣና ተወዳዳሪ እንደጠፋ ቢገለጽም ጨረታ ስለመውጣቱ ለኦዲት ስራው የቀረበ ማስረጃ የለም፡፡ በተጨማሪ በአካባቢው ያሉ ይህን አገልግሎት መስጠት የሚችሉት እነዚህ ድርጅቶች

ብቻ ስለመሆናቸው የቀረበ ማስረጃ የለም፡፡ በመሆኑም በግዥ መመሪያው መሰረት ግዥ ስለመፈጸሙ ተገቢው ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡

<u>የስራ አመራሩ ምላሽ፤</u>

በኦዲት ማሻሻያ ሀሳብ ላይ የመኪና ኪራይ አገልግሎት እና የአይሲቲ እቃዎች ግዥ መመሪያው መሰረት ከአቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ ከተመዘገቡት መካከል ፍትሃዊ በሆነ ምርጫ ቢያንስ አምስት ተወዳዳሪዎች ስለመረጣቸው ማስረጃ አልቀረበም በሚል ለቀረበው በግዥ ኤጀንሲ የአቅራቢዎች ዝርዝር ላይ የተመዘገቡ እና በስራ ላይ ያሉትን በመጋበዝ የተደረገ ውድድር ነው፡፡ ግዥ አጄንሲ በአቅራቢ ዝርዝር የተመዘገቡበትን የሚገልፅ ማስረጃ አባሪ (3) ተያይዟል፡፡

የመስተንግዶ አገልግሎት ግዥን በተመለከተ በጋምቤላ፣ በጅጅጋ፣ በአፋር እና በቤንሻንጉል ጉሙዝ ብ/ክ/መንግሰታት በሚገኙ ዋና የክልል ከተሞች ደረጃውን የጠበቀ አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ሆቴሎች ጥቂት መሆናቸውን ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር በሀገሪቱ የሚገኙ ሆቴሎችን ደረጃ የሚገልጽ ሰነድ አስመልክቶ ያወጣውን ዝርዝር እና በግዥ ኤጀንሲ አቅራቢዎች ዝርዝር የተመዘገቡትን ዝርዝራቸውን በማየት የተፈለገውን አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ሆቴሎች ጥቂት በመሆናቸው በዋጋ ማቅረቢያ በማወዳደር የተፈፀመ ግዥ ነው ፡፡

<u>የኦዲተሩ አስተያየት፤</u>

ከግዥ ኤጀንሲው የአቅራቢ ዝርዝር ውስጥ ምን ያህል የመኪና ኪራይ አቅራቢዎች እንዳሉና ከነዚህ ውስጥ ደግሞ በምን መስፈረት እነዚህ ድርጅቶች ለውድድር እንደቀረቡ የሚያሳይ ማስረጃ አልቀረበም፡፡ የመስንግዶ አገልግሎትን በሚመለከት በዛ ክልል ወይም ከተማ የሆቴል አገልግሎቱን ሊሰጡ የሚችሉት ድርጅቶች በውድድር ውስጥ የተካተቱት ብቻ ስለመሆናቸው ማስረጃ አልቀረበም፡፡

2.3. ግኝት፤<u>በተቋሙ ስም ላልተመዘገበ ስልክ የአገልግሎት ክፍያ ወጪ የሆነ ብር 61,521.33</u>

የፌደራል መንግስት መ/ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል 2 ተራ ቁጥር 8(2/ለ)የወጪ ሂሳብ ወጪ ከመደረጉ በፊት ስለወጪው የተሟላ ማስረጃ ማቅረብና ስልጣን ባለው አካል መፈቀድ አለበት ይላል፡፡ በዚሁ መሰረት በተቋሙ ስም የስልክ መስመሮች ለተሰጠ አገልግሎት ብቻ ክፍያ የተፈጸመ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ የተቋሙ ስልክ ናቸው ተብለው በቀረበው የስልክ ቁጥሮች ዝርዝር

ውሰጥ ባልተካተቱ የስልክ መስመሮች በድምሩ ብር 61,521.33 የፍጆታ ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

ስጋት፤

- ለተቋሙ አገልግሎት ላልዋሉ የስልክ አገልግሎት ክፍያዎች ሊፈጸሙ ይችላሉ፡፡
- የተፈቀደው በጀት ለመ/ቤቱ አገልግሎት ላይውል ይችላል፡፡

የማሻሻየ ሀሳብ፤

ከጠቅላላ አገልግሎት በቀን 24/12/2013 በተሰጠን የጽሁፍ ማስረጃ መሰረት በመ/ቤቱ ስም የሚገኙ የስልክ ቁጥሮች ዝርዝር መሰረት የተጠቀሱት የስልክ ቁጥሮች በዝርዝሩ የሌሉ በመሆኑ ምላሹን አልተቀበልነውም፡፡ በመሆኑም ክፍያ እንዲከፈል የፈቀደው ኃላፊ ሊጠየቅና አለአግባብ የተከፈለው የስልክ ክፍያም ተመላሽ ሊደረግ ይገባል፡፡

የስራ አመራሩ ምላሽ፤

ሁሉም የስልክ እና ዳታ መስመሮች በመ/ቤቱ ስም የተመዘገቡ ስለመሆናቸው ለማረጋገጥ ጥረት የተደረገ ሲሆን የስልክ እና የዋይፋይ አጠቃቀም የውስጥ መመሪያ በሚፈቅደው መሰረት በዴሊቨሪ ዩኒት የተመደቡ የሚኒስትር አማካሪዎች እና የበላይ አመራሮች የስልክ እና የዳታ መስመሮች መሆናቸውንና ሁሉም ቁጥሮች በመ/ቤቱ ድህረ-ክፊያ አካውንት የተመዘገቡ ናቸው፡፡ ይህንኑ የሚያስረዳ አባሪ 4 ተያይዟል፡፡

የኦዲተር አስተያየት፤

በቀረበው ማስረጃ መሰረት ዴሊቨሪ ዩኒት የተመደቡ እና የሚንስቴሩ አማካሪ መሆናቸው ቢገለጽም በዴሊቨሪ ዩኒት ስምምነት ተብሎ በቀረበው ማስረጃ ውስጥ ስም ዝርዝራቸው የሌለ መሆኑ እንዲሁም የሚኒስትሩ አማካሪ ተብለው ከቀረቡት ዝርዝሮች ውስጥ የዶ/ር ስዩም እና ክቡር እስማኤል ስልክ በድምሩ ብር 5635.08 ከተሰጠው ዝርዝር ጋር የተረጋገጠ ሲሆን ቀሪው ብር 61,521.33 ማስረጃ አልቀረበለትም፡፡ በመሆኑም ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚጠቀምባቸው ስልኮች በአግባቡ ተለይተው በመመሪያው መሰረት ስልክ ሊይዙ የሚገባቸው ብቻ እንዲይዙ ሊደረግ ይገባል በተጨማሪ አለአግባብ ክፍያ የተፈጸመባቸው ስልክ ቁጥሮች ተጣርተው በተሰጠው የማሻሻያ ሃሳብ መሰረት እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

2.4. ግኝት፤ የበጀት ዓመቱን ያልጠበቀ የወጪ ሂሳብ ብር 719,904.59

የፌደራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 አንቀጽ 14/1 እና 2 የመደበኛና የካፒታል የሥራ መስኬጃ ወጪዎች ሲፈጸሙ፤ ወጪው ለሚደረግበት ተግባር በበጀት ዓመቱ የተያዘ ወይም ወጪውን ለመሸፈን ቀሪ በጀት መኖሩንና ወጪው በመስራያ ቤቱ ዕቅድ ውስጥ የተያዘና በጥሬ ገንዘብ ፍላጎት እቅድ ላይ የተካተተ መሆኑ ሳይረጋገጥ ክፍያ መፈጸም እንደማይገባ ይገልጻል፡፡ ይሁን እንጂ የበጀት አመቱ የሂሳብ እንቅስቃሴ በበጀት ዓመቱ ውስጥ የሚከፈል መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡፡

የ2012 በጀት ዓመት ግንቦት፤ሰኔ እና የሚያዝያ ወር 2012 የስልክ አገልግሎት ክፍያ በሂሳብ መደብ 2241108/6258 በዕቅድ ሳይያዝና በጀት ሳይጠየቅ ለ2013 በጀት ዓመት ከተፈቀደው በጀት ለዘመን ቴሌኮም ኃ/የተ/የግ ማህበር በቀን 23/2/13 በቫውቸር ቁጥር 17893 ብር 395,249.14 እንዲሁም በቀን 13/12/2012 በቫውቸር ቁጥር 324,655.45 በድምሩ ብር 719,904.59 በጀት ዓመቱን ሳይጠብቅ ክፍያ ተፈጽሞና በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

ስጋት፤

- የፋይናንስ መግለጫው የበጀት ዓመቱን ትክክለኛው ወጪ ላያመለክት ይችላል፡፡
- መመሪያዎች ተግባራዊ ላይደረጉ ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ፤

የክፍያ ጥያቄ የሚቀርበው ዘግይቶ በመሆኑ የተፈጠረ ነው ቢባልም የበጀት ዓመቱ ከመጠናቀቁ በፊት ለድርጅቱ ጥያቄ በማቅረብ ክፍያ ሊፈጸም ይገባል፡፡ ይህ አሰራር አስቸጋሪ ከሆነም በሚቀጥለው በጀት ዓመት ላይ ተገቢው በጀት እንዲያዝ ሊደረግ ይገባል፡፡

የስራ አመራሩ ምላሽ፤

በኦዲት ማሻሻያው የተሰጠው አስተያየት በበጀት ላይ ከሚያስከትለው ጫና አንጻር ተገቢና ተክክለኛ በመሆኑ በቀጣይ የሚታረም መሆኑን እየገለጽን ችግሩ የተፈጠረው ዘመን ተሌኮም ከሚባል ድርጅት ጋር በነበረው የስራ ውል መሰረት ድርጅቱ በወቅቱ የክፍያ ጥያቄ ባለማቅረቡ የተፈጠረ ሲሆን ክፍያው ሊዘገይ የቻለው ከኢትዮ ቴለኮም የሚመጣው የክፍያ ጥያቄ አብዛኛውን ጊዜ ዘግይቶ በመሆኑ ከዘመን ተሌኮም ጋር የነበረውን ውል ተደጋጋሚ ማስጠንቀቅያ በመስጠት እዲቋረጥ በማድረግ በቀጥታ

ከኢትዮ ቴሌኮም ጋር ወርሃዊ ክፍያ በመፈፀም ላይ እንገኛለን የማስተካከያ እርምጃ ተወስዷል፡፡

2.5 ግኝት፤ <u>ለተቋሙ አገልግሎት ስለመዋሉ ማረጋገጥ ያልተቻለ የስልክ ፍጆታ ክፍያ ወጪ የሆነ ብር 55,176.38</u>

መ/ቤቱ የካቲት 2012 ባወጣው የስልክ፣ሲዲኤምኤ፣የመስተንግዶ እና አላቂ እቃዎች አጠቃቀም መመሪያ መሰረት ክፍያዎች የሚፈፀሙ መሆኑን ለማረጋገጥ በናሙና ኦዲት ሲደረግ፤ በመ/ቤቱ የሰው ሀይል ዝርዝር ውስጥ ላልተካተቱ እና የመ/ቤቱ ሰራተኞች ላልሆኑ ግለሰቦች ለተጠቀሙበት የስልክ አገልግሎት ብር 55,176.38 ክፍያ ተፈፅሞ ተገኝቷል፡፡

<u>ስጋት፤</u>

የመንግስት ገንዘብ ለታቀደለት አላማ ላይውል ይችላል፡፡

<u>የማሻሻያ ሀሳብ፤</u>

በዴሊቨሪ ዩኒት ለሚሰሩ ለሚኒስቴር አማካሪዎች የተፈፀመ ክፍያ መሆኑ በተሰጠው ምላሽ ቢገለፅም መመሪያው ላይ በተጠቀሰው መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ የሚኒስቴር አማካሪ ስለመሆናቸው እና በመ/ቤቱ የሰው ሀይል ዝርዝር ውስጥ ስለመካተታቸው ማስረጃ እንዲቀርብ ወይም አለአግባብ የተከፈለው ክፍያ ከሚመለከታቸው ግለሰቦች ተመላሽ ሊደረግ ይባል፡፡

<u>የስራ አመራሩ ምላሽ፤</u>

በሚኒስቴር መ/ቤቱ በዲሊቨሪ ዩኒት በተለያየ ሙያ በፕሮጀክት ተቀጥረው ለተላኩ የሚኒስትር አማካሪዎች የውስጥ መመሪያው በሚፈቅደው መሰረት የተከፈለ የስልክና የኢንተርኔት ክፍያ መሆኑን እየገለጽን የሚኒስትር አማካሪዎች ስለመሆናቸው የሚገልጸውን ሰነድ በአባሪ -7-- አያይዘን አቅርበናል፡፡

<u>የኦዲተሩ አስተያየት፤</u>

ለዴሊቨሪ ዩኒት በተለያየ ፕሮጀክት ተቀጥረው በልዩ ልዩ ሙያ የሚንስትሩ አማካሪዎች እንደሆኑ ቢገለጽም እነዚህን ባለሙያዎች የላከው አካል እና ተቋሙ ምንም አይነት ውል ያልገቡ በመሆኑ የስልክ አገልግሎት ክፍያው ለተቋሙ አገልግሎት ስለመዋሉ ማረጋገጥ የማያስችል በመሆኑ ለወደፊቱ እንደዚህ አይነት አገልግሎቶች ሲከናወኑ

በተቋሙና አማካሪዎችን በሚልከው ድርጅት መካከል ግልጽ የሆነ ስምምነት ሊፈጸም ይገባል፡፡

2.6. ግኝት፤ በተገቢው የሂሣብ መደብ ያልተመዘገበ የወጪ ሂሳብ ብር 7,048,052.89

የፌዴራል መንግሥት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ዓ.ም. በክፍል ሁለት አንቀፅ 6 ተራ ቁጥር 4 ላይ የመንግስት መስሪያ ቤቶች በበጀት አደረጃጀት ሥርዓት መሠረት የተፈቀደላቸው በጀትና የወጣውን ወጪ በሚያሳይ መልኩ ተለይቶ በተሰጠ የበጀት መለያ መደብ ተጠቅመው የሂሳብ እንቅስቃሴያቸውን መመዝገብ እንዳለባቸው ይገልጻል:: በዚሁ መሰረት ሚ/ር መ/ቤቱ ምዝገባውን የሚያከናውን መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በተለያዩ የወጪ ማስመስከሪያዎች የተከፈሉ በድምሩ ብር 7,048,052.89 በተገቢው የሂሳብ መደብ ሳይመዘገቡ ተገኝተዋል፡፡

ስጋት፤

- ወጪዎች በተገቢው የወጪ ሂሳብ መደብ ተመዝግበው ሪፖርት ካልተደረጉ የመ/ቤቱ የሂሳብ ሪፖርት ትክክለኛ ገፅታ ላያሳይ ይችላል፡፡
- የሂሳብ አያያዙ የበጀት አጠቃቀም ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ያሳድራል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ፤

ምዝገባዎች በፌደራል መንግስት የሂሳብ አወቃቀር ስርአት መሰረት ስለመከናወናቸው ተገቢው ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡

የስራ አመራሩ ምላሽ

የሥራ አመራሩ የማሻሻያ ሃሳቡን ተቀብሎታል፡፡

2.7 ግኝት፡- የግዥ መመሪያን ያልተከተለ የውስን ጨረታ ግዥ ብር 2,163,810.00

በውስን ጨረታ የሚፈጸም ግዥ ላይ በጨረታው ተሳታፊ ሊሆን የሚችሉ አቅራቢዎች ቁጥር በርካታ ቢሆኑም በመመሪያው በተቀመጠው ገደብ ውስጥ ከሆነ ከአቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ መካከል **ፍትሃዊ** በሆነ ምርጫ ቢያንስ አምስት እጩ ተወዳዳሪዎችን

መምረጥ እንደሚቻል ይገልጻል፤ በዚሁ መሰረት ፍትሀዊ ውድድር መደረጉን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

በቀን 13/09/2013 በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 22190 በሂሳብ መደብ 2221102/6232 ለመስክ መኪና ኪራይ ከጥረት የመኪና ማከራየትና ፕሮሞሽን በብር 704,000.00 እንዲሁም ለየአይሲቲ እቃዎች ግዥ በቀን 30/10/13 በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 23964 በሂሳብ መደብ 2211108 (6218) ብር 1,249,360.00 እንዲሁም በሂሳብ መደብ 2211102 (6212) ብር 210,450.00 በድምሩ ብር 2,163,810.00 ከታቦር ቴክኖሎጂ ሶሉሺንስ ኃላ/የተ የግ.ማህበር በውስን ጨረታ ግዥ የተፈጸመ ሲሆን፤ ከአቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ ፍትሃዊ በሆነ መንገድ ተወዳዳሪዎች ስለመጋበዛቸው የሚያሳይ ማስረጃ ባለመቅረቡ የግዥውን ፍትሃዊነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

<u>ስጋት፤</u>

ፍትሃዊ ውድድር ላይከናወን ይችላል፡፡

<u>የማሻሻያ ሃሳብ፤</u>

በመመሪያው መሰረት በአቅራቢነት ዝርዝር ውስጥ ከተመዘገቡት መካከል የአቅራቢዎች ዝርዝር ሊለይና ከነዚህ ውስጥ ደግሞ አምስት ተወዳዳሪዎች በምን መስፈርት እንደተመረጡ ሊያሳይ የሚችል ማስረጃ ሊቀርብ ይገባል፡፡

<u>የስራ አመራሩ ምላሽ፤</u>

በኦዲት ማሻሻያ ሀሳብ ላይ ከአቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ ከተመዘገቡት መካከል ፍትሃዊ በሆነ ምርጫ ቢያንስ አምስት ተወዳዳሪዎች ስለመረጣቸው ማስረጃ አልቀረበም በሚል የተሰጠውን አስተያየት በተመለከተ በመንግስት ግዥ ኤጅንሲ የአቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ የተመዘገቡ እና በስራ ላይ ያሉትን በመጋበዝ የተደረገ ውድድር ነው፡፡ በግዥ አጀንሲ በአቅራቢ ዝርዝር የተመዘገቡበትን የሚገልፅ ማስረጃ አባሪ (10) ተያይዟል፡፡

<u>የኦዲተሩ አስተያየት፤</u>

በአቅራቢ ዝርዝሮች ውስጥ ከተዘረዘሩት መካከል በምን መስፈርት እንደተመረጡ የሚያሳይ ማስረጃ ባለመቅረቡ ግዥው ፍትሃዊ ውድድርን ያሳፈነ ስመሆኑ ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

3. የተሰብሳቢ ሂሳብ፤

3.1 ግኝት፤በወቅቱ ያልተወራረደ ተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 278,865,668.05

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 32፣የፌደራል መንግሥት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 እንዲሁም በፌዴራል የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 መሰረት ቅድሚያ ክፍያዎች በወቅቱ የሚወራረዱ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡፡

- በ4210 (5217109) የሂሳብ መደብ ብር 70,819,888.58 1 ዓመት የቆየ፤
- በ4253 (5217205) የሂሳብ መደብ ብር 168,095,583.46 1 ዓመት የቆየ፤እንዲሁም ብር 39,950,196.01 ከአምስት እስከ አሰር አመት የቆየ፤

በድምሩ ብር 278,865,668.05 በወቅቱ ያልተወራረደ ሂሳብ መኖሩ በኦዲት ወቅት ተረጋግጧል፡፡

ስጋት፤

- በተሰብሳቢ ሂሳቦች ላይ ተገቢውን ቁጥጥርና ክትትል ካልተደረገ የመንግሥት ገንዘብ ሳይሰበሰብ ሊቀር ወይም ለብክነት ሊዳረግ ይችላል፡፡
- በመመሪያው መሰረት በወቅቱ እንዲወራረድ አለመደረጉ የተሰብሳቢ ሂሳብ ክምችት እንዲኖር ሊያደርግ ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

በተሰብሳቢ የተያዙ ሂሣቦች በወቅቱ እንዲወራረዱ ተገቢው ቁጥጥርና ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡

የሥራ አመራሩ ምላሽ፤

የተሰብሳቢ ሂሳብን በተመለከተ በቀረበው አስተያየት መሠረት ቁጥጥርና ክትትል እየተደረገ የሚገኝ ሲሆን ረጅም ዕድሜ ያላቸውን ከመዝገብ እንዲሰረዙ ኮሚቴ ተዋቅሮ እየተሰራ ይገኛል ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የክልሎች ልዩ ድጋፍ ስራዎች ወደ መስኖና ቆላማነት ሚኒስቴር ስለተዘዋወሩ የፕሮጀክቶቹ ተሰብሳቢ ሂሳብ ከፍተኛ ሲሆን ከሰላም ሚኒስቴር የሂሳብ መዝገብ ላይ የሚቀነስ ይሆናል፡፡

4.ተከፋይ ሒሳብ፤

4.1.ግኝት፤በወቅቱ ያልተከፈለ የተከፋይ ሂሳብ በድምሩ ብር 123,715,072.74

በፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 8 ንኡስ አንቀጽ 5 በተመለከተው መሰረት ተከፋይ ሂሳቦችን ለመከታተል ተገቢው የቁጥጥር ስርዓት መዘርጋቱንና ሂሳቡም በወቅቱ መከፈሉን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፤ ሰኔ 30/2013 በቀረበው የሂሳብ ሪፖርት መሠረት፤

- በሂሳብ መደብ 6174299 (5054)ብር 107,307,453.31፤
- በሂሳብ መደብ 6172105 (5006) ብር 1,157,527.65፤
- በሂሳብ መደብ 6172112 ብር 115,173.00፤
- በሂሳብ መደብ 6172202 (5002) ብር 13,198,150.33፤
- በሂሳብ መደብ 6173117(5028) ብር 1,676,650.67፤
- በሂሳብ መደብ 6174208 (5059) ብር 260,117.78፤

በድምሩ ብር 123,715,072.74 በወቅቱ ለባለመብቱ ሳይከፈል ተገኝቷል፡፡

ስጋት፤

የተከፋይ ሂሳቦቹ በወቅቱ ካልተከፈሉ የዕዳ ክምችት ሊበዛ ስለሚችል በጥሬ ገንዘብ ፍላጎት ላይ ተፅእኖ ሊያሳድር የሚችል ከመሆኑም በተጨማሪ በቆይታ ብዛትና በማስረጃ ዕጦት ተገቢ ያልሆነ ክፍያ ሊፈጸም ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

ለባለድርሻ አካላት ክፍያ መፈጸሙን እንዲሁም ለአንዳንዶቹ ሂሳቦች ማስተካከያ እንደተደረገ ቢገለጽም ስለመከፈሉም ሆነ ተገቢው ማስተካከያ ስለመደረጉ ማስረጃ ባለመቅረቡ ምላሹን አልተቀበልነውም፡፡በመሆኑም ተከፋይ ሂሳቦች ለባለመብቶቹ በወቅቱ እንዲከፈሉ የሚመለከተው አካል ጥብቅ ቁጥጥርና ክትትል ማድረግ ይኖርበታል፡፡

የስራ አመራ ምላሽ፤

የተከፋይ ሂሳብን በተመለከተ በቀረበው አስተያየት መሠረት ቁጥጥርና ክትትል እየተደረገ የሚገኝ ሲሆን ረጅም ዕድሜ ያላቸውን ከመዝገብ እንዲሰረዙ ኮሚቴ ተዋቅሮ እየተሰራ ይገኛል ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የክልሎች ልዩ ድጋፍ ስራዎች ወደ መስኖና ቆላማነት

ሚኒስቴር ስለተዘዋወሩ በየክልሎቹ የሚገኙ ፕሮጀክቶቹ ተከፋይ ሂሳብ ከፍተኛ በመሆኑ ከሰላም ሚኒስቴር የሂሳብ መዝገብ ላይ የሚቀነስ ይሆናል ፡፡

5.<u>በጀት፤</u>

5.1.ግኝት፤ <u>ያልተሰራበት በጀት ብር 720,554,921.68</u> <u>እና ከበጀት በላይ ወጪ የሆነ ብር 5,187,185.58</u>

በፌዴራል መንግሥት የበጀት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 2/2003 እና በፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ቁጥር 190/2002 ክፍል 3 አንቀጽ 12 መሠረት መ/ቤቶች የተመደበላቸውን በጀት በአግባቡ በሥራ ላይ ሊያውሉ እንደሚገባቸው ይገልፃል፡፡ በተጨማሪ በፌዴራል መንግስት የገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት 6/2 ላይ የበጀት ዝውውር ወይም ተጨማሪ በጀት ካልተፈቀደ በስተቀር ለአንድ የመንግስት መ/ቤት በሂሳብ መደብ ተለይቶ ከተፈቀደው በጀት በላይ ወጪ መፈጸም እንደማይቻል ይገልጻል፡፡ ይሁን እንጂ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የ2013 በጀት ዓመት የበጀት አጠቃቀም ኦዲት ሲደረግ፤ በበጀት አመቱ ለመደበኛና ለካፒታል የተፈቀደው በጀት ሥራ ላይ ከዋለው ጋር ሲነፃፀር በየሂሳብ መደቦቹ ከተመደበው ከ10% በላይ ሥራ ላይ ያልዋለ ሲሆን፤

- ለመደበኛ ወጪዎች ከተፈቀደው በጀት ብር 1,158,849,645.52 ውስጥ ብር 434,075,023.35 ወይም 37.5%፤
- ለካፒታል ወጪዎች ከተፈቀደው ብር 800,000,000.00 ውስጥ ብር 286,479,898.33 ወይም 35.8%

በድምሩ ብር 720,554,921.68 ስራ ላይ ያልዋለ በጀት ሲሆን፤

<u>ከበጀት በላይ የወጣ</u>

- በመደበኛ በጀት በሁለት የሂሳብ መደቦች በድምሩ ብር 5,187,185.58 ከበጀት በላይ ወጪ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

<u>ስጋት፤</u>

- በጀቱ በእቅዱ መሠረት ሥራ ላይ እንዲውል አለመደረጉ የሚ/ር መ/ቤቱ ዓመታዊ የሥራ ውጤት ዝቅ የሚያደርግ ከመሆኑም በተጨማሪ የበጀት ዕቅዱን ትክክለኛነት ላያመለክት ይችላል፡፡
- የበጀት ዝውውር ሣይደረግ ወይም ተጨማሪ በጀት ሳይፈቀድ ከተፈቀደው በጀት በላይ መጠቀም መመሪያን ከመጣሱም ባሻገር ተጠያቂነትንም ያስከትላል፡፡

<u>የማሻሻያ ሀሳብ፤</u>

አገሪቷ ያላትን ውስን በጀት በማብቃቃት በተገቢው ስራ ላይ ማዋል ይቻል ዘንድ ባለ በጀት መ/ቤቶች ጥቅም ላይ የማይውል በጀት በመጠየቅ የሌላውን መ/ቤት መሠረታዊ መርሀግብር እንዳይደናቀፍ በእቅድና በፕሮግራም ላይ የተመሰረተ በጀት ሊይዙ ይገባል፡፡ በተጨማሪ ከበጀት በላይ ወጪ እንዳይደረግ በመመሪያው መሰረት የበጀት ዝውውር በማድረግ ስራ ላይ ማዋል ሲገባ ከበጀት በላይ ወጪ መደረጉ ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም የተፈቀደው በጀት በአግባቡ በስራ ላይ ሊውል ይገባል፡፡

<u>የስራ አመራሩ ምላሽ</u>

1. <u>ስራ ላይ ያልዋለ በጀት ብር 1,958,849,645.52 ምክንያቶች፡-</u>

   መደበኛ በጀት ብር 434,075,023.35 _በተመለከተ፡-

- ✓ አርባ ሺ የፖሊስ ሰራዊት ለማሰልጠን የታቀደ ቢሆንም በወቅቱ ከነበረው የሃገሪቱ ወቅታዊ ሁኔታ አንጻር ስልጠናውን መስጠት ያልተቻለ በመሆኑ፡፡ አብዛኛው በክልሎች ሊካሄዱ የታቀዱ የምክክርና የውይይት መድረኮች በነበረው ወቅታዊ ሁኔታ መድረኮቹ ባለመካሄዳቸው በጀቱን መጠቀም አልተቻለም፡፡

ካፒታል በጀት ብር 286,479,898.33 በተመለከተ፡-

- ✓ በ2013 በጀት ዓመት የበጐ ፍቃድ ማህበረሰብ ልማት ኘሮግራም 50ሺ ተሳታፊዎችን ለማሰልጠን የታቀደ ቢሆንም በወቅታዊ ሁኔታ ምክንያት ማሰልጠን የተቻለው 10ሺ ብቻ መሆኑ እንዲሁም የብሄራዊ መታወቂያ ኘሮግራም ለቋሚ እቃ ግዢ የተያዘው በጀት የውጭ ግዢ ሂደት ባለመጠናቀቁና ክፍያ ባለመፈፀሙ በጀቱን ሰራ ላይ ማዋል አልተቻለም፡፡

2. <u>ከበጀት በላይ ወጪ የሆነ ብር 5,187,185.58 በተመለከተ፡-</u>

- ✓ በበጀት ኮድ 6241 ለተሽከርካሪዎች ጥገና ከበጀት በላይ ወጪ የሆነው በአማራ ክልልና በአፋር ክልል 18 ተሽከርካሪዎች ግንባር ለ8 ወራት በመቆየታቸው ግማሾቹ በጥይት

ስለተመቱ ሞተርና ቦዲ የተቀየረበት እንዲሁም ጠቅላላ ሰርቪስ እና እድሳት የተደረገበት ሆኖ ይህም በበጀት ዝውውር የተሸፈነ ነው፡፡ እንዲሁም የመስሪያ ቤቱ አብዛኛው ተሽከርካሪዎች ያረጁ በመሆናቸው ከመ/ቤቱ የስራ ባህሪ ጋር የሚጣጣም ተሽከርካሪ ባለመኖሩ ለጥገና ወጪ የዋለ በጀት ነው፡፡

- ✓ በበጀት ኮድ 6258 የቴሌኮሚኒኬሽን አገልግሎት ክፍያዎች በወቅቱ ባለመጠየቃቸው የ2012 በጀት ዓመት ክፍያ ጥያቄ በ2013 በጀት ዓመት መፈፀሙ፡፡

በአጠቃላይ የ2013 ዓም በጀት አመት የሚኒስቴር መ/ቤቱ ስራዎች የፕሮጀክት ስራዎች በመሆናቸው በቅደመ ክፍያ ተፈጽሞባቸው ወደ ወጪ የሚቀየሩት በ2014 ዓ/ም በጀት ዓመት በመሆኑ በጀቱ ስራ ላይ ሳይውል ቀርቶ ሳይሆን የብሄራዊ መታወቂያ ፕሮጀክት ፣ የብሄራዊ በጎ ፈቃድ ፕሮጀክት እና የክልል ልዩ ድጋፍ ስራዎች አገልግሎቱ ወይም ዕቃው ሲቀርብና ሲጠናቀቅ በሚመለከታቸው የስራ ክፍሎች እየተረጋገጠ ወደ ወጪ የሚቀየር በመሆኑ ምክንያት የተፈጠረ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

<u>የኦዲተር አስተያየት፤</u>

የ2012 በጀት ዓመት የቴሌኮሚኒኬሽን አገልግሎት ክፍያ በወቅቱ አለመፈፀሙ በ2013 በጀት ዓመት ከበጀት በላይ ወጪ ለመደረጉ ምክንያት መሆኑ በተሰጠው የስራ አመራር ምላሽ ቢገለፅም አገልግሎቱ በተገኘበት በጀት ዓመት ክፍያ እንዲፈፀም አለመደረጉ እንዲሁም በተቋሙ የስልክ ቁጥሮች ዝርዝር ውስጥ ባልተካተቱ የስልክ መስመሮች ክፍያ መፈፀሙ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የተፈቀደለትን በጀት በመመሪያው መሰረት በስራ ላይ አለማዋሉን ያመለክታል፡፡

ለተሽከርካሪዎች ጥገና ከበጀት በላይ ወጪ የተደረገው በበጀት ዝውውር የተሸፈነ ነው የሚል ምላሽ በስራ አመራሩ ቢሰጥም የበጀት ዝውውር ተደርጎ የሚፈፀም ክፍያ በጀቱ ወጪ በሚደረግበት የሂሳብ መደብ ዝውውር የተደረገው በጀት የሚተከል ወይም በተፈቀደ በጀት የሚያዝ በመሆኑ ከበጀት በላይ ወጪ ሆኖ የማይታይ በመሆኑ የተሰጠው ምላሽ ተቀባይነት የለውም፡፡ በተጨማሪም የበጀት ዝውውር በማድረግ ክፍያ መፈፀሙ በተሰጠው ምላሽ ቢገለፅም ማስረጃ አልቀረበም፡፡

6.<u>ንብረት፤</u>

6.1.ግኝት፤<u>የንብረት አያያዝ እና አጠባበቅን በተመለከተ</u>

የሚኒስቴር መ/ቤቱ የንብረት አስተዳደር እና አጠባበቅ በመንግሥት የንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 እና ይህንኑ ለማስፈፀም በወጣው የመንግሥት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 መሰረት የሚከናወን መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ፤

- የንብረት መጋዘን ውስጥ ቋሚና አላቂ እቃዎች፤ የሚወገዱና የማይወገዱ በአንድ የንብረት መጋዘን ውስጥ ተቀላቅለው ተገኝተዋል፡፡
- መወገድ የሚገባቸው ወንበሮች፤ ጠረጴዛ፤ ፋይልካቢኔት እና ኮፊ ቴብል ኮምፒውተር የመሳሰሉት ሳይወገዱ ለቁጥጥር በማይመች መልኩ ተከማችተው ተገኝተዋል፤
- ብዛት ያላቸው የመኪና ጎማዎች፤ የመኪና መለዋወጫ ዕቃዎች፤ ፈርኒቸሮች (የኃፊዎች፤ የባለሙያ እና የእንግዳ ወንበሮች)፤ ጠረጴዛዎች፤ጋቢ እና የደንብ ልብሶች እቃ ግምጃ ቤት ውስጥ ለቁጥጥር በማይመች መልኩ የተቀመጡ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

<u>ስጋት፤</u>

- አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ንብረቶች በአቀማመጥና በአወጋገድ ችግር ምክንያት ለምዝበራና ለብልሽት ሊዳረጉ ይችላሉ፡፡

<u>የማሻሻያ ሀሳብ፤</u>

መወገድ የሚገባቸው ንብረቶች በመመሪያው መሰረት ሊወገዱና አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ንብረቶች ለአስተዳደር በሚመች መልኩ ተለይተው ሊቀመጡ ይገባል፡፡

<u>የስራ አመራሩ ምላሽ፤</u>

በኦዲት ምርመራው ማሻሻያ ሀሳብ የተሰጠው አስተያየት ተገቢና ትክክለኛ መሆኑን ተቀብለን አስፈላጊው የእርምት ርምጃ እየተወሰደ የሚገኝ ሲሆን ልተወገዱ ንብረቶች በአጭር ጊዜ ውስጥ ለማስወገድ እንቅስቃሴ የተጀመረ ሲሆን አስወጋጅ ኮሚቴ በአዲስ መልክ ተደራጅቶ ስራ ጀምረዋል፡፡ በዚህ መሰረት ያልተወገዱ ቋሚ ንብረቶች በበላይ አመራር ውሳኔ መሰረት በስጦታ በአዲስ መልክ ለተቋቋሙ ክልሎች እና በጦርነት ጉዳት ለደረሰባቸው ክልሎች በመንግስት ንብረት አስተዳደር መመሪያ መሰረት እየተላላፈ ይገኛሉ፡፡

- ከንብረቶች አቀማማጥ ጋር የተነሳው የኦዲት አስተያየት በኦዲት ወቅት ቋሚ ንብረቶች መጋዘን በሌሎች ንብረቶች የተሞላ በመሆኑ የተወሰኑ የህፃናት ማቆያ

ንብረቶች በአላቂ እቃዎች መጋዘን ተከማችቶ ተገኝተዋል ፡፡ ስለሆነም በአሁኑ ሰዓት በአስተያየቱ መሰረት የማስተካካያ ርምጃ ተወስደዋል፡፡

➢ ጎማዎች ሌሎች ብረታብረቶችን በጨረታ ለማስወገድ በንብረት አስወጋጅ ኮሚቴ አማካይነት ስራ ተጀምረዋል፡፡

በቀጣይም ቀሪ ንብረቶችን በተፋጠነ ሁኔታ በማስተላላፍ ፍፃሜ የሚያገኝ ይሆናል፡፡ የተላለፉ ንብረቶችና የበላይ አመራር ውሳኔ አባሪ 10፡፡

6.2. ግኝት፤ <u>የተሽከርካሪ አያያዝና አስተዳደር በተመለከተ፤</u>

የመሥሪያ ቤቱ የተሽከርካሪ ሥምሪት፣ አያያዝና አጠቃቀም በፌዴራል መንግሥት የተሽከርካሪዎች ስምሪትና አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 32/2004 መሰረት መፈጸሙን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

- በሚ/ር መ/ቤቱ ስም የባለቤትነት መታወቂያ ያልተዘጋጀላቸው በተለያየ መ/ቤት ስም የተመዘገቡ 85 ተሽከርካሪዎች መኖራቸው፣
- የሰሌዳ ቁጥር 4-21970 የጠፋ ተሽከርካሪ፣ 4-13113፤4-03397 የወደሙ በአጠቃላይ በበላይ አመራሩ ውሳኔ ሳይሰጣቸው መገኘታቸው፣
- ይወገዳሉ ተብሎ ወደ ሌላ መ/ቤት የተላለፉ ስምንት ተሽከርካሪዎች የመጨረሻ ውሳኔ አለመታወቁ፤
- የሰሌዳ ቁጥር UN1609፤ 4-17076፤ 4-22452 እና 4-08387 የባለቤትነት መታወቂያ (ሊብሬ) የሌላቸው ተሽከሪካሪዎች መገኘታቸው፣

በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

<u>ስጋት፤</u>

- ተገቢው የቁጥጥር ስርዓት ላይዘረጋ ይችላል በዚህም ንብረቶቹ ከመ/ቤቱ ቁጥጥር ውጭ ሊሆኑና ለምዝበራ ሊዳረጉ ይችላሉ

<u>የማሻሻያ ሀሳብ፤</u>

የባለቤትነት መታወቂያቸው በሌሎች መ/ቤቶች ስያሜ የሚገኙ መኪኖች ወደ መ/ቤቱ የሚዛወሩበት ሁኔታ ሊመቻች ይገባል፡፡ የጠፉ፣ የወደሙ እንዲሁም የሚወገዱ

ተብለው የተያዙ ተሽከርካሪዎች በንብረት አስተዳደር መመሪያ መሰረት ውሳኔ ሊያገኙ ይገባል፡፡

<u>የስራ አመራሩ ምላሽ</u>

የንብረት አስተዳደር እና ጠቅላላ አገ/ት ዳይሬክቶሬት ምላሽ፤-

- ሊብሬ የሌላቸው ተሽከርካሪዎች
  1. UN1609
  2. 4-17076
  3. 4-22452
  4. 4-08387

ከላይ ከተራ ቁጥር 1-3 የተጠቀሱት ተሽከርካሪዎች የበላይ አመራሩ የሚጠቀማቸው ሲሆን ተሽከርካራቹ የተላኩት ከጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት በመሆኑ የባለቤትነት ደብተር እንዲላክልን በተደጋጋሚ ጠይቀን ሊላክልን አልቻለም፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ ሁለቱ ተሽከርካሪዎች የቀድሞ የሰላም ሚኒስትሯ ወደ ሌላ ሚኒስቴር መ/ቤት ተሹመው ሲሄዱ ከአነአሽከርካሪዎቹ ይዘው የሄዱ በመሆኑተመላሽ እንዲያደርጉ በድብዳቤ የተጠየቀ ቢሆንም እስከዛሬ አልተመለሰም፡፡ በተራ ቁጥር 4 የተመለከተው ተሽከርካሪ ከገንዘብ ሚኒስቴር የተሰጠንና ሊብሬውም እዚያው የሚገኝ በመሆኑ ለማስመጣት ጥረት እየተደረገ ይገኛል፡፡

- በሶማሌ ክልል በተፈጠረው ግጭት የቀረ ተሽከርካሪ ሰሌዳ 4-21970

ወደ ሶማሌ ክልል ለስራ በሄደበት 2010ዓ.ም በነበረው ሀገራዊ የፀጥታ ችግር ምክኒያት በሶማሌ ክልል ጅግጅጋ ከተማ በመቅረቱ ተሽከርካሪውን በሚመለከት የውሳኔ ሀሳብ ለበላይ አመራሩ ቀርቦ ተሽከርካሪው ለክልሉ እንዲጸላለፍ ስምምነት ተደርጎ በቀጣይ ከመዝገብ ተሰርዞ በስጦታ እንዲተላላፍ ለማድረግ በሂደት ላይ ይገኛል፡፡

7.<u>ልዩ ልዩ፤</u>

7.1. <u>ግኝት፤ የግዥ ዕቅድ ቢዘጋጅም በተቋሙ የበላይ ኃላፊ ሳይጸድቅ ለግዢ ኤጀንሲ የተላከ መሆኑን፤</u>

ሰኔ 2002 ዓ.ም የወጣው የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ክፍል 3 አንቀፅ 8 ቁጥር1 ማንኛውም የመንግስት መ/ቤትና በስሩ የተደራጁ አካላት የታቀዱ የስራ

ፕሮግራሞቻቸውን ተግባራዊ ለማደረግ የሚያስፈልጋቸውን ግዥ በወቅቱ ለመፈጸም የሚያስችል በመርሃ ግብር የተደገፈ የግዥ ዕቅድ ማዘጋጀት እንደሚገባ ይገልፃል፡፡ስለሆነም መ/ቤቱ በመመሪያው መሰረት የግዥ ዕቅድ በማዘጋጀት ግዥ የሚፈፅም መሆኑን ለማረጋጋጥ ኦዲት ሲደረግ፤የ2013 በጀት ዓመት የግዥ ዕቅድ ቢዘጋጅም በተቋሙ የበላይ ኃላፊ ያልጸደቀ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ተረጋግጧል፡፡

<u>ስጋት፤</u>

- የተቋሙ ፕሮግራሞች ተግባራዊ ላይደረጉ ይችላሉ፡፡
- መ/ቤቱ የተፈቀደለትን በጀት ለታለመለት ዓላማ ላያውል ይችላል፡፡
- ግዥዎች በመመሪያው መሰረት ላይፈፀሙ ይችላሉ፡፡

<u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

ለወደፊቱ የበጀት ዓመቱን የግዢ ዕቅድ በተቋሙ የበላይ ኃላፊ እንዲፀድቅ በማድረግ በዕቅዱ መሰረት ግዥዎች እንዲፈፀሙ መደረግ ይኖርበታል፡፡

<u>የስራ አመራሩ ምላሽ፤</u>

የ2013 በጀት ዓመት የግዥ እቅድ ቢዘጋጅም በተቋሙ የበላይ ሃለፊ አልፀደቀም የተባለው ትክክል መሆኑን የተቀበልን ሲሆን ችግሩ የታየው በወቅቱ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ሃላፊዎች ለወቅታዊ የፀጥታ ስራ ሀገራዊ ስምሪት ወስደው አ/አበባ አካባቢ ባለመኖራቸው የግዥ እቅድ ከሚዘገይ በፋይናንስ ግዥ ሃለፊው ተፈርሞ እንዲላክ ተደርጓል፡፡ በኦዲት ማሻሻያ ሀሳብ ላይ ለወደፊቱ የበጀት ዓመቱ የግዥ እቅድ በተቋሙ የበላይ ሃለፊ እንዲፀድቅ በማድረግ በዕቅድ መሰረት ግዥዎች እንዲፈፀሙ መደረግ ይኖርበታል የተባለውን ሀሳብ ተቀብለን በቀጣይ ትምህርት ወስደን የምናስተካክለው ይሆናል፡፡

8. <u>ክትትል ኦዲት፤</u>

8.1<u>ግኝት፤እርምጃ ያልተወሰደባቸው የ2012፤የ2011፤የ2010፤እና የ2009 በጀት ዓመት የኦዲት ግኝቶች፤</u>

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ማቋቋሚያ አዋጅን ለማሻሻል በወጣ አዋጅ ቁጥር 982/2008 ክፍል አምስት አንቀጽ 17/3 መሰርት ተመርማሪ መሥሪያ ቤቶች በፌዴራል ዋናው ኦዲተር በተላኩ ሪፖርቶች በተገለፁ ግኝቶች ላይ ተገቢውን የእርምት እርምጃ እንዲወስዱ በተሰጡ የማሻሻያ ሃሣቦችና አስተያየቶች መሠረት ከ15 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ እርምጃ የመውሰድ ግዴታ እንዳአለባቸው ይገልጻል፡፡በዚሁ መሰርት ለሚ/ር

መ/ቤቱ 2012 በጀት ዓመት ኦዲት ሪፖርት በተሰጠው አስተያየት መሠረት እርምጃ ስለመወሰዱ በ2013 በጀት ዓመት ኦዲት ሲደረግ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ግኝቶች የማስተካከያ እርምጃ ሳይወሰድ ተገኝቷል።

መግለጫ	እርምጃ ለወሰድበት የሚገባ		እርምጃ የተወሰደበት			እርምጃ ያልተወሰደበት		
ኦዲት የተደረገበት በጀት ዓመት	በገንዘብ መጠን	በቁጥር	በገንዘብ መጠን	በቁጥር	በመቶኛ (በ%)	በገንዘብ መጠን	በቁጥር	በመቶኛ (በ%)
2012	432,311.85		0.00	0	0	432,311.85	3	100
2011	48,822,849.07	4	0.00	0	0	48,160,346.18	4	100
2010	2,899,618.93	8	0.00	0	0	1,738,801.38	8	100
2009	1,698,478.13	13	0.00	0	0	3,180,357.35	13	100
	53,853,257.98	27		0		53,853,257.98	27	

የ2012 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶች

- ለገቢ ሂሳብ ብር 84,840.00 መነሻ የሆነው የሰነድ ማስረጃ እንዲቀርብ አስተያየት ቢሰጥም ማስረጃው አልቀረበም ፤
- በመመሪያ ከተቀመጠው የስልክ ክፍያ ገደብ በላይ የተከፈለ ብር 317,750.24 ከሚመለከታቸው ግለሰቦች ተመላሽ እንዲደረግ አስተያየት ቢሰጥም ገንዘቡ ያልተመለሰ መሆኑ
- ከሚመለከተው አካል ፈቃድ ሳይገኝ የተፈጸመ የትርፍ ሰዓት ክፍያ ብር 29,321.613 ተመላሽ እንዲደረግ እንዲሁም ማስረጃ ያልቀረበላቸው ማስረጃ እንዲቀርብ አስተያየት ቢሰጥም ገንዘቡ ያልተመለሰና ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ

የ2011 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶች

- ከቤት አበል ተቀናሽ ያልተደረገ ግብር ብር 20,700.00 ከግለሰቦቹ ላይ ተሰብስቦ ለመንግስት ገቢ እንዲደረግ አስተያየት ቢሰጥም ያልተሰበሰበ መሆኑ፤
- የተሟላ የወጪ ማስረጃ ያልቀረበለት የስልክ አገልግሎት ክፍያ ብር 660,491.89 ማስረጃ እንዲቀርብ አስተያየት ቢሰጥም ማስረጃዎቹ አለመቅረባቸው ፤

- በብልጫ የተከፈለ ውሎ አበል በድምሩ ብር 410,024.00 ከግለሰቦቹ ተመላሽ እንዲደረግ አስተያየት ቢሰጥም ተመላሽ ያለመደረጉ፤
- በመ/ቤቱ ስም ላልተመዘገበ የሞባይል ስልክ ወጪ የሆነ የአገልግሎት ክፍያ በድምሩ ብር 5,274.17 ተመላሽ እንዲደረግ አስተያየት ቢሰጥም ተመላሽ አለመደረጉ፤
- ለኦዲት ያልቀረቡ ሰነዶች ብር 47,724,348.01 ማስረጃቸው እንዲቀርብ በኦዲት አስተያየት ቢሰጥም ማስረጃ አለመቅረቡ፤

<u>የ2010 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶች</u>

- ሰራተኞች ላልሰሩባቸው ቀናት በድምሩ ብር 26,423.80 አለአግባብ ተከፍሎ በመገኘቱ ከሚመለከታቸው ግለሰቦች ተመላሽ እንዲደረግ አስተያየት ቢሰጥም ገቢ አለመደረጉን፤
- ከንብረት ክፍል ወጪ ሆነው አገልግሎት ላይ ያልዋሉ የመኪና ጎማዎች ግዥ ብር 96,600.0 አገልግሎት ላይ ባለማዋላቸው የሚመለከታቸው ሃላፊዎች ተጠያቂ ስለመሆናቸው ማስረጃ አልቀረበም፡፡
- ንብረቶች ገቢ ሳይደረጉ የተፈፀመ ክፍያ ብር 858,731.08 በሚመለከት ንብረቱ ለመ/ቤቱ አገልግሎት ለመዋሉ ማረጋገጫ እንዲቀርብ ወይም ገንዘቡ ከሚመለከተው አካል ተመላሽ እንዲሆን አስተያየት ቢሰጥም ተመላሽ አለመደረጉ
- አለአግባብ ለውሎ አበል የተከፈለ በድምሩ ብር 66,934.40 ከሚመለከታቸው ሠራተኞች እና የስልጠና ተሳታፊዎች ተመላሽ እንዲደረግ አስተያየት ቢሰጥም ተመላሽ አለመደረጉ
- ለአየር ትኬት በድጋሚ የተከፈለ ብር 67,321.00 እና የተሟላ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገበ ብር 1,781,598.65 በመመሪያው መሠረት ለወጪው ተገቢው ማስረጃ ሊቀርብ ወይም ገንዘቡ ከሚመለከታቸው ተመላሽ ሊደረግ እንደሚገባ አስተያየት ቢሰጥም ገንዘቡ ገቢ አለመደረጉን ማስረጃዎችም አለመቅረባቸው ታውቋል፡፡

<u>የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶች</u>

- የነዳጅ ግዥና ለሠልጣኞች የትራንስፖርት አበል በድምሩ ብር 89,229.15 የክፍያ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ ሂሳብ በመመዝገቡ ህጋዊ ማስረጃ እንዲቀርብለት አስተያየት ቢሰጥም ማስረጀ አለመቅረቡ ፡፡

- በቀን 19/11/2008 በቫውቸር ቁጥር 290312 በሂሳብ መደብ 6233 በሠዓት መቆጣጠሪያው መሠረት የተሣታፊ ቁጥር 48 ሠራተኞች ሆነው ሳለ ለመስተንግዶ ክፍያ ሲፈጸም ለ170 ሠራተኞች በመሆኑ በልዩነት የ122 ሠራተኞች ብር 46,311.00 ክፍያ የተፈጸመ ሲሆን የተሳታፊዎች ብዛት እና ስም ዝርዝር /አቴንዳንስ/ እንዲሁም የውል ስምምነት እንዲቀርብ በኦዲት አስተያየት ቢሰጥም ማስረጃ አለመቅረቡ፤

- በቀን 23/09/2009፣ በቫ.ቁጥር /የባንክ የወጪ ማስመስከሪያ/ 290946፣ በሂሳብ መደብ 6271፣የተከፈለው ለኢትዮጵያ ሥራ አመራር ኢንስቲትዩት ብር 35,185.80 ለስልጠና የተከፈለ ክፍያ ሲሆን የመጠየቂያ ደብዳቤ፣ የተሳታፊዎች ብዛት እና ስም ዝርዝር /አቴንዳንስ/ እንዲሁም የውል ስምምነት ለኦዲት ስራ እንዲቀርብ ቢጠየቅም ማስረጃ አለመቅረቡ
- በሂሳብ መደብ 6231 የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 654004 በቀን 29/07/2009 ለቤንሻንጉል ጉሙዝ ስልጠና ወጪ ከሆነው ውስጥ ተመላሽ ለብር 1,270.00 የገቢ ደረሰኝ ያልተቆረጠ፤ የተሳታፊዎች የመገጣጠሚያ ደብዳቤ ያልቀረበ መሆኑ፤ የደሞዝ መጠንም ያልተገለጸና በሰዓት መቆጣጠሪያ ላይ ለ8 ቀን ተፈርሞ እያለ ክፍያ የተፈፀመው ግን ለ13ቀን መሆኑ በዚህ ምክንያት የ5 ቀን ብር ማለትም 5*177*30=26,550.00 በብልጫ የአበል ክፍያ ተከፍሎ መገኘቱ፤

  በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 653963 በቀን 09/06/2009 በድሬደዋ ለተካሄደው ስልጠና የመገጣጠሚያ ደብደቤ አለመኖሩ፣ ለተሳታፊዎች በሠዓት መቆጣጠሪያው መሠረት የ3ቀን አበል መከፈል ሲገባው ለ7 ተሳታፊዎች የ2 ቀን ማለትም 2*214*7= 2,996.00 ብልጫ ተከፍሎ በመገኘቱ፤

  በቀን 22/05/2009 በሀዋሳ ከተማ ለተካደው ስልጠና በወጣው ወጪ ለየክልሉ የመገጣጠሚያ ደብዳቤ አለመኖሩ ፣ የሰዓት መቆጣጠሪያ ላይ ያለው ማስረጃ የ2ቀን ሲሆን ለሰልጣኞች የተከፈለው የውሎ አበልና ትራንስፖርት ከ3ቀን እስከ 6 ቀን በመሆኑ ያለአግባብ ብር 127,929.00 በብልጫ ተከፍሎ በመገኘቱ፤

በድምሩ ብር 157,475.00 ያለአግባብ የተከፈለው ገንዘብ ተመላሽ እንዲደረግ ወይም ክፍያውን ከፈቀደው ኃላፊ ተመላሽ እንዲያደርግ አስተያየት ቢሰጥም እርምጃ አለመወሰዱ፤

- መ/ቤቱ የአገልግሎትና የዕቃ ግዥ ፈጽሞ በተለያዩ 9 የወጪ ቫውቸሮች የተሟላ ደጋፊ ማስረጃ ሳይኖር በድምሩ ብር 284,588.36 ክፍያ በመፈጸሙ ቀሪ ማስረጃዎች እንዲቀርቡ አስተያየት ቢሰጥም እርምጃ አለመወሰዱ፤
- ከግንቦት/2009 ዓ.ም - ሰኔ 2009 ዓ.ም ብር 11,185,435.72 ወጪ የተደረገባቸው የክፍያ ሰነዶች በወቅቱ ለኦዲት ባለመቅረባቸው ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ ያልተቻለ ሲሆን፤ በ2010 በጀት ዓመት ኦዲት ብር 10,171,238.34 ለኦዲት ሥራ በመቅረቡ በኦዲት ቡድኑ የታየ ሲሆን ቀሪው ብር 1,014,197.38 ማስረጃው ባለመቅረቡ የሂሳቡን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ባለመቻሉ ማስረጃዎቹ ተፈልገው ሊቀርቡ እንደሚገባና በውስጥ ኦዲት በኩልም ሰነዶቹ ተጣርተው ሪፖርት ሊቀርብ እንደሚገባ አስተያየት ቢሰጥም እርምጃ ያለመወሰዱ፤
- የትራንስፖርት ወጪ በሚል በቫውቸር ቁጥር 22470 በቀን 26/12/2007 ዓ.ም ከወጣው ብር 30,229.25 ውስጥ ብር 11,872.50 ምንም የወጪ ማስረጃ ያልቀረበለት፣ለመብራት አገልግሎት የተከፈለ ብር 4,499.51 ቢል ያልቀረበለት እና የትራንስፖርት የተከፈለ ብር 5,342.00 በድምሩ ብር 21,714.01 ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ በመመዝገቡ ማስረጃ እንዲቀርብ ቢጠየቅም አለመቅረቡን፤
- የመ/ቤቱ ሰራተኞች ለአጭር ጊዜ ስልጠና እንዲሰጣቸው ለግዥ አገልግሎት ድርጅት ለዘጠኝ ሰልጠኞች በሚል ብር 39,409.35 ቅድሚያ ክፍያ ተፈጽሞ ነገር ግን ስልጠናውን የወሰዱት አራት ሠራተኞች ብቻ ሲሆኑ የአምስቱ ሠራተኞች በድምሩ ብር 19,400.00 ስልጠናውን ሳይወስዱ ለግዥ አገልግሎት ድርጅት ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡
- የሴቶችና ወጣቶች ጽ/ቤት ለማርች 8 ባዘጋጀው ፕሮግራም ላይ በሰዓት መቆጣጠሪያው መሠረት የተሳታፊ ቁጥር 141 ሰራተኞች ሆኖ ሳለ ለመስተግዶ ክፍያ ሲፈጸም ለ216 ሰራተኞች ክፍያ የፈጸመ በመሆኑ በልዩነት የ75 ሰዎች ብር 8,250.00 በብልጫ ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡
- ከመ/ቤቱ ለተሰናበቱ ሰራተኛ ለወ/ሮ እየሩሳሌም አስፋው ብር 2,691.63 ፣አቶ ጎይቶመ ጽጋብ ብር 5,478.80 ፣ ወ/ሮ ቃልኪዳነ ካሳ ብር 2875.17፣ ወ/ሮ አመለወርቅ ጉዲሳ ብር 1,846.88፣ አቶ ታጁ ሙክታር ብር 4,791.67፣ ሰለሞን ያይንሸት ብር 2,779.78 እና ብርሀኑ ሀይሉ ብር 1,663.50 በድምሩ ብር **22,127.43** መ/ቤቱ ከለቀቁ በኋላ በተለያየ ጊዜ ደሞዝ ተከፍሏቸው ተገኝቷል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ፤

በኦዲት ግኝቶች ላይ በተሰጡት የማሻሻያ ሃሳቦች መሰረት አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ በተደጋጋሚ በኦዲት ሪፖርቶች ቢገለፅም ሚ/ር መ/ቤቱ በተሰጡት የኦዲት አስተያየቶች ላይ በወቅቱ እርምጃ ባለመውሰዱ የሥራ አመራሩ ተጠያቂ ሊደረግ ይገባል፡፡ በመሆኑም በኦዲት ሪፖርት በሚሰጡት የማሻሻያ ሃሳቦች መሰረት እርምጃ ለመወሰዱ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንደሚገባው በድጋሚ እናሳስባለን፡፡

የስራ አመራሩ ምላሽ

የክትትልና ድጋፍ ምላሽ፡-

የ2012 በጀት ዓመት ሂሳብ በተመለከተ፡-

- **ገቢ ሂሳብ ብር 84 840.00 መነሻ የሆነው የሰነድ ማሽረጃ እንዲቀብር አስተያየት ቢሰጥም ማስረጃው አልቀረበም፡፡**

ከሃይማኖት ድርጅቶችና ማህበራት ምዝገባ አገልግሎት የሚሰበሰብ ገቢ ወደ ፋይናንስ ስራ ክፍል ሲላክ ሲስተም ላይ ስለገቢው አይነት በግልጽ የተቀመጠ ነገር ባይኖርም በሌሎች የዋጋ ተመንና ዝርዝር የክፍያ መጠን ላይ የገቢው ምክንያት በግልጽ የተጻፈ ሲሆን በታሪፍ መሰረት ለስንት ወርና ዓመት የፍቃድ እድሳትና የሪፖርት መዘግየት ቅጣት ገቢ እንደተሰበሰበ በደረሰኞቹ ላይ አለመገለጹ እንደ ትምህርት ወስደን ለእነዚህ የገቢ ሂሳቦች መነሻ የሆነው የሰነድ ማስረጃ ሊቀርብ እና ሊረጋገጥ ይገባል ለሚለው የስራ ክፍሉ ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች በሚኒስትሮች ም/ቤት የፀደቀውን የአገልግሎት ክፍያ ተመን መመሪያ በወቅቱ ለምርመራው ስራ የቀረበ ቢሆንም አሁንም ስለተወሰደው እርምጃ ፡፡ ከስራ ክፍሉ የሚላከውን የገቢ ማዘዣ ትዕዛዝ ናሙና እንዲሁም በሚኒስቴሮች ም/ቤት የፀደቀውን መመሪያ ቀደም ስል በአባሪነት የላክን ቢሆንም በድጋሚ በአባሪ ቁጥር -- አያይዘን አቅርበናል፡፡

የ2012 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶች

በመመሪያ ከተቀመጠው የስልክ ክፍያ ገደብ በላይ የተከፈለ ብር 317,750.24 በሚል የቀረበውን የኦዲት ግኝት በተመለከተ ችግሩ የተከሰተው በዓለም ላይ ብሎም በሀገራችን በተከሰተው የኮቪድ -19 ወረርሽኝ ምክንያት አብዛኛው አመራርና ሠራተኞች እቤታቸው ሆነው የሚሰጣቸውን ስራ እንዲሰሩ በመደረጉ ምክንያት ተደጋጋሚ የሆኑ የስልክ

ግንኙነቶች ሲደረጉ ስለነበር እና ከተለያዩ የአረብ ሀገራት ዜጎቻችን ወደ አገራቸው እንዲመለሱ በመደረጉ ምክንያት እነዚህን ዜጎች የመቀበል ኃላፊነት ለሚ/ር መ/ቤታችን በመሰጠቱ ምክንያት ከአቅም በላይ በሆነ የስራ ምክንያት መሆኑን የተቋሙ ከፍተኛ አመራሮች ተቀብለው ውሳኔ የሰጡበት መሆኑን እየገለጽን ችግሮቹን በመፈተሽ የውስጥ መመሪያውን የማሻሻል ስራ እየሰራን መሆኑን፤ የከፍተኛ አመራሮች የስልክና የዳታ መስመሮች ያለገደብ እንደምጠቀሙ በመመሪያው የተቀመጠ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

የተሟላ ማስረጃ ባለመቅረቡ የክፍያውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ የትርፍ ሰዓት ክፍያ ብር 29,321.61 በሚል ለቀረበው የኦዲት ግኝት የተሰጠ ምላሽና አስተያየት

የትርፍ ሰዓት ክፍያ ከመፈፀሙ በፊት ስራውን ገብተው እንዲሰሩ በአመራሩ የተሰጠ ትዕዛዝና ሰራተኞቹም ገብተው ስለመስራታቸው የሚያረጋግጥ የሰዓት መቆጣጠሪያ ፎርማ ሊዘጋጅና በማስረጃነት ሊቀርብ ይገባል በሚል ለተሰጠው የማሻሻያ አስተያየት የተገለፁት ቅድመ ሁኔታዎች የተሟሉ ስለመሆናቸው ማስረጃዎቹን አያይዘን በአባሪ ------ ማቅረባችንን እንገልፃለን ፡፡

የ2011 በጀት ዓመት ሂሳብ በተመለከተ፡-

1. **ከቤት አበል ላይ ተቀናሽ ያልተደረገ ግብር በድምሩ ብር 20,700 ተገኝቷል፡፡**

<u>**መልስ፤**</u>

የሰራተኞች ወርሀዊ ክፍያ በሚዘጋጅበትና ከክፍያው ላይ የተለያዩ ተቀናናሾች በተቀናጀ የሂሳብ አስተዳደር ስልት /IFMIS/ በሚመዘገቡበት ወቅት ሲስተሙ ከአራቱ የተቋሙ ሰራተኞች የቤት አበል ላይ የገቢ ግብር እንዲያሰላ ባለመደረጉ የተፈጠረ ስህተት ቢሆንም በኦዲት በተሰጠን ማሻሻያ ሃሳብ መሠረት ከተቋሙ አራት ሰራተኞች ላይ ሳይቀነስ የቀረው የቤት አበል የስራ ግብር በ2013 በጀት ዓመት ከደመወዛቸው ተቀንሶ ገቢ ተደርጓል፡፡ በአባሪ 13 ማቅረባችንን እንገልጻለን

2. **በብልጫ የተከፈለ ውሎ አበል ብር 410,024.00 ከግለሰቦች ተመላሽ እንዲደረግ አስተያየት ቢሰጥም ተመላሽ አላደረጉም፡-**

ለተባለው በወቅቱ ምላሽ እንደተሰጠው ከተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ተውጣጥተው በግጭት ቅድመ ማስጠንቀቂያ እና በሰላም እሴት ርእሰ ጉዳዮች ዙሪያ በአንቦ ከተማ በተከናወነው

የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ላይ ለተሳታፊዎች አለአግባብ የተከፈለ ክፍያ የለም የሚል ምላሽ ተሰጥቷል።

3. **በመስሪያ ቤቱ ስም ላልተመዘገበ የሞባይል ስልክ የአገልግሎት ክፍያ ብር 5,274.17፡-**
በተሰጠው አስተያየት መሰረት ደብዳቤ በመፃፍ ከግለሰቦቹ ደመወዛቸው ላይ በመቀነስ ተመላሽ እንዲደረግ ተደርጓል።

4. **ያልቀረቡ ሰነዶች ብር 47,724,348.01 ማስረጃ ያልቀረበባቸው የተባለው**
ሰነዱን ካለበት በማስፈለግ እንዲወጣና ተጣርተው ሚላሽ የሚሰጥ ይሆናል።

- **የ2010 በጀት ዓመት ሂሳብ በተመለከተ፡**

1. **አላግባብ የተከፈለ ደመወዝ ብር 26 423.80 ተመላሽ አልተደረገም የሚለውን በተመለከተ፡-**

ወ/ሮ ማርታ አድማሱ አለግባብ ከተከፈላቸው ደምወዝ ብር 19,882.2 ውስጥ።

- በቀን 01/04/2011 በገቢ ደረሰኝ ቁጥር 0001835 ብር 2,000
- በቀን 30/04/2011በገቢ ደረሰኝ ቁጥር 0001838 ብር 3,000
- በቀን 06/07/2011 በገቢ ደረሰኝ ቁጥር 0002027 ብር 2,000

በድምሩ ብር 7,000 ተመላሽ ያደረጉ መሆኑን የሚያሳይ ሪፖርት በመኖሩ ቀሪውን ተመላሽ ያልተደረገ ከሰው ሀብት ልማት ጋር በመነጋገር የአቶ ያለው ከበደ ለገሰ እና የአቶ ጌታሁን ከበበ ጎንፋ ደሞዝ አገዳ ድብዳቤ ከደረሰው ጀምሮ የሂሳብ ክፍሉ ምንም አይነት ክፍያ ለግለሰቦቹ ያልከፈለ መሆኑን እየገለጽን ሰራተኞቹ የእገዳ ደብዳቤው ለሂሳብ ክፍሉ ከመጻፉ በፊት ያለአግባብ በድምሩ ብር 6,541.6 ወስደዋል የተባለውን ገንዘብ ለማስመለስ ከሰው ሃብት ልማት ጋር መረጃ በመውሰድ የሚጣራ ይሆናል።

2. **ከንብረት ክፍል ወጪ ሆነው አገልግሎት ላይ ያልዋሉ የመኪና ጎማዎች ግዥ ብር 96,600.00 በተመለከተ፡-**

ጉዳዩ በተቋሙ የህግ ክፍል በኩል ክስ ተመስርቶ በወንጀልና በፀረ ሙስና ተይዞ ክትትል እየተደረገበት ያለ ሲሆን በቀጣይ በህግ የሚሰጠው ውሳኔ ሲደርስ የምናሳውቅ ይሆናል።

3. **ንብረቶች ገቢ ሳይደረጉ የተፈፀመ ክፍያ ብር 858,731.08 በተመለከተ፡-**

ህትመቶች ፣ ምንጣፎች እና የቢሮ ጠረጴዛዎች የገቢ ደረሰኝ ተቆርጦላቸው ወደ ንብረት ክፍል ገቢ መደረጉን ማወቅ ተችሏል።

4. **አለአግባብ የተከፈለ የውሎ አበል ብር 66,934.40 በተመለከተ፡-**

- ለአቶ ፍቅረማሪያም አጥላው ያለአግባብ የተከፈለ የአንድ ቀን የውሎ አበል ገንዘብ በቀን 04/06/2011 በቁጥር 0001879 በተመዘገበ ሰነድ ብር 291.21 ተመላሽ እንዲሆን ተደርጓል፡፡

  ቀሪ ሦስት ሠራተኞች ተመላሽ አላደረጉም ለተባለው ቀደም ሲል የነበረ በመሆኑ ሰነዱን በማጣራት ላይ ሲለሚገኝ ማጣራቱ እንደ ተጠናቀቀ ተመላሽ ይደረጋል፡፡

የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ በተመለከተ፡-

1. **በ2009 ለነዳጅ ግዥና ለሠልጣኞች የትራንስፖርት አበል በድምሩ ብር 89,229.15 ክፍያ ሲፈጽም ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ ሂሳብ ተመዝግቧል፡፡**

- በኢትዮጲያ ሶማሌ ክልል ፊልቱ ዞን በመስክ ስራ ላይ ለነበረ የተቋሙ ተሽከርካሪ በበጀት አመቱ ለነዳጅ ከተከፈለው ብር 35,502.45 ውስጥ በአካባቢው የነዳጅ ማደያ ባለመኖሩ በችርቻሮ ዋጋ ለነጋዴዎች ከማደያ ዋጋ በላይ በልዩነት የተከፈለው ብር 6,506.00 የነዳጅ ግዥውን ያከናወኑት ባለሙያ አቶ ዘነበ ሆንጃ ገንዘቡን ተመላሽ አድርገው ወደ ብሄራዊ ባንክ ፈሰስ ተደርጓል፡፡ፈሰስ የተደረገበትም ሰነድ እንዲያያዝ ተደርጓል፡፡
- ለችግሩ መፍትሄ ለመስጠት በተወሰደ እርምጃ ከነዳጅ ማደያዎች ርቀው በመስክ ስራ ላይ የሚገኙ የተቋሙ ተሽከርካሪዎች ከ2010 በጀት አመት ጀምሮ ማደያዎች ከሚገኙባቸው አካባቢዎች ነዳጅ በጀሪካን ይዘው በመሄድ ተግባራቸውን እንዲያከናውኑ ወይም ሌሎች ህጋዊ አማራጮችን እንዲጠቀሙ መመሪያ ተሰጥቷል፡፡

<u>በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የተወሰዱ የማስተካከያ እርምጃዎች፡-</u>

- ከግንቦት/2009 እስከ ሰኔ/2009 ያሉ የወጪ ማስመስከሪያ ማስረጃዎችን(የሂሳብ ሰነዶች) በሙሉ በኦዲት ምርመራ ወቅት ዝግጁ ያደረግን ቢሆንም ተቋሙ ከግንቦት 2009 ጀምሮ ቀድሞ ሲጠቀምበት የነበረውን የሂሳብ መረጃዎች አያያዝ በመተው ወደ አዲስ የተቀናጀ የሂሳብ መረጃ አስተዳደር ስርአት(IFMIS) በመግባቱ በኦዲት ምርመራው ወቅት የቀረቡትን የሁለት ወራት የሂሳብ ሰነዶች ከአዲሱ የሂሳብ መረጃ አያያዝ ስርአት ጋር በማጣጣም ሂደት የተፈጠረ ክፍተት ነበር፡፡

  የሂሳብ ሰነዶች ለምርመራ እንዳልቀረቡ ተደርጎ የቀረበው ግኝት ከላይ በጠቀስነው ችግር ምክንያት የመጣ በመሆኑን እና ከነዚህ ሰነዶች መካከል በኦዲተር ታይተውና ተፈርሞባቸው እንደሌሉ ተቆጥሮ ሪፖርት የተደረጉት ጭምር እንዳሉበት ገልጸን

በፌደራል ዋና ኦዲተር እንዲቀርቡ የተጠየቁ የብር **11,185,435.72**(አስራ አንድ ሚሊዮን አንድ መቶ ሰማኒያ አምስት ሺ አራት መቶ ሰላሳ አምስት ብር ከሰባ ሁለት ሳንቲም) የወጪ ማስመስከሪያ ሰነዶቹ በሙሉ ተደራጅተው መዘጋጀታቸውን ለፌደራል ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት ሪፖርት በማድረግና ሰነዶቹን በግንባር አቅርቦ ለተቋሙ ለማሳየት ጥያቄ ቀርቦ የ2010 በጀት አመት የሚኒስትር መስሪያ ቤቱን የሂሳብ ሰነዶች የመግቢያ የሂሳብ ምርመራ እያካሄዱ የሚገኙ የዋናው ኦዲተር መስርያ ቤት ኦዲተሮች እንዲያዩት ይደረጋል የሚል ምላሽ በተሰጠን መሰረት ከዚህ ቀጥሎ ከተራ ቁጥር 1 — 37 የተዘረዘሩና ማስረጃ እንዲቀርብባቸው የተጠየቁ የተለያዩ የገንዘብ መጠን የያዙ ሰነዶችን ለፌደራል ዋና ኦዲተር ባለሙያዎች አሳይተን ሰነዶቹ በአግባቡ ተደራጅተው መቀመጣቸውን እንዲያረጋግጡ ተደርጓል፡፡

በአግባቡ ተደራጅተው ለብቻቸው የተቀመጡና መኖራቸው በኦዲተሮች የተረጋገጡ ሰነዶች ዝርዝር ከዚህ እንደሚከተለው ወደ ሲስተም ከገቡበት የሂሳብ መረጃ አስተዳደር ስርአት (IFMIS) ቁጥራቸው ጋር ከገጽ **14 - 18** በሰንጠረዥ ቀርበዋል፡፡

2. **<u>በቀን 23/09/2009 በቫት ቁጥር የባንክ የወጪ ማስተካከያ በሂሳብ መደብ 6271 ለኢትዮጵያ ስራ አመራር ኢንስቱትዩት የተከፈለ ው ብር 35185.80 በተመለከተ፡</u>**

ለሪከርድ እና ማህደር 3 ሰራተኞች ከጥር 29/2009 እስከ የካቲት 10/2009 ለተከታታይ 12 ቀናት ስልጠና ለወሰዱበት ለእያንዳንዳቸው **11,728.60** በድምሩ **35,185.80** ለኢትዮጲያ ስራ አመራር ኢንስቲትዩት የተከፈለ ክፍያ ነው፡፡

የሰው ኃይል ልማትና ንብረት አስተዳደር ለኢትዮጲያ ስራ አመራር ኢንስቲትዩት የጻፈውን የስልጠና መጠየቂያ እንዲሁም ለእያንዳንዱ ሰልጣኝ መከፈል ያለበትን ዋጋ እና የገቢ ማድረጊያ የባንክ ቁጥር በመጥቀስ ስልጠና ለሚሰጠው ተቋም ገቢ እንዲደረግ ለእቅድ ዝግጅት ክትትልና ግምገማ ዳይሬክቶሬት የጻፋቸውን ደብዳቤዎች፣ የተሳታፊዎች ብዛት እና ስም ዝርዝር/አቴንዳንስ/ የያዙ ሰነዶች ከክፍያ ደረሰኙ ጋር እንዲያያዙ ተደርጓል፡፡

ለስልጠና ተቋሙ ቅድመ ክፍያ የተፈጸመው ተቋሙ ለሚሰጣቸው ስልጠናዎች የቁርጥ ክፍያ/Down payment/ የሚያስከፍል በመሆኑ እና በቀን 20/04/2009 በቁጥር H3-858-0011-09-6 የተሳታፊዎች ብዛት እና የስልጠና ርእሶች ተጠቅሶ ለኢንስቲትዩቱ የተጻፈውን ደብዳቤ እንደውል በመቁጠር ሲሆን በተወሰደ የማስተካከያ እርምጃ ከ2011 በጀት አመት

ጀምሮ ኢንስቲትዩቱ ለተቋማችን በሚሰጠው የስልጠና መርሃ-ግብሮች የውል ስምምነት ሰነድ ሳይፈረም የስልጠና ቁርጥ ክፍያ/Down payment/ ተፈጻሚ እንዳይሆን ተደርጓል፡፡

3. **በሂሳብ መደብ ቁጥር 6231 የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 654004 በቀን 29/07/2009 ለቤንሻንጉል ጉሙዝ ስልጠና ወጪ ከሆነው ብር 1270.00 ተበመለከተ፡-**

- በተሰጠው የኦዲት ማሻሻያ ሃሳብ መሰረት ተመላሽ በማድረግ ብር 1,270.00 የገቢ ደረሰኝ ተቆርጦለታል፡፡ የክፍያ ሰነዱም ተያይዞ ይገኛል፡፡

- በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት የተከናወነውን የመንደር ማሰባሰብ መርሃ ግብር የማህበረሰብ ተጠቃሚነት ለመገምገም የዳሰሳ ጥናት በተከናወነበት ወቅት ከክልሉ የተለያዩ ወረዳዎች ተውጣጥተው የጥናቱ ተሳታፊ ለነበሩ ባለሙያዎች የ13 ቀናት አበል የተከፈለ ሲሆን እነኝህ ባለሙያዎች ወደ አሶሳ ከተማ የመጡት ራቅ ካሉ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ወረዳዎች በመሆኑ በጥናቱ ላይ ለቆዩበት 8 ቀናት አቴንዳንስ ፈርመው እንዲሁም ከየወረዳዎቹ ሲመጡ የደርሶ መልስ ጉዞ ላደረጉባቸው 5 ቀናት አቴንዳንስ ሳይፈርሙ በድምሩ የ13 ቀናት አበል እንዲከፈላቸው የተደረገ ሲሆን ክፍያው የተፈጸመው ለስራው በቀረበው ፕሮፖዛል መሰረት ስለነበር የጥናቱ ተሳታፊዎች የመገጣጠሚያ ደብዳቤ አልተያያዘም፡፡ በ2010 በጀት አመት በተሰጡ ስልጠናዎች የተሳታፊዎችን ወርሃዊ ደሞዝ እና የመጡበትን አካባቢ የሚገልጽ የመገጣጠሚያ ደብዳቤ ክስልጠና ክፍያ ሰነዶች ጋር እንዲያያዝ ተደርጓል፡፡

- በድሬዳዋ ከተማ በተካሄደ ስልጠና ለተሳተፉ ሰልጣኞች የ3 ቀናት አበል ሲከፈል ለ7ቱ የስልጠናው ተሳታፊዎች ግን ሁለት ቀናት ተጨምሮ የ5 ቀናት አበል ተከፍሏል ለተባለው ግኝት፣ ሰባቱ ሰዎች የተለያዩ የስልጠና ቅድመ ሁኔታዎችን ለማመቻቸት ስልጠናው ከመጀመሩ ከሁለት ቀናት በፊት ቀደም ብለው በስልጠና ቦታው በመገኘታቸው ያንን ታሳቢ ያደረገ ክፍያ እንጂ ከሌሎች ተሳታፊዎች በተመሳሳይ ቀናት በቦታው ተገኝተው ለነሱ በተለየ መልኩ ሁለት ቀን ተጨምሮ አልተከፈለም፡፡

- በሀዋሳ ከተማ በተካሄደ ስልጠና ለተሳታፊዎች የመገጣጠሚያ ደብዳቤ አልቀረበም ለተባለው አስተያየት የ2008 በጀት አመት የኦዲት ምርመራ ሲካሄድ የመገጣጠሚያ ደብዳቤ እንደሚያስፈልግ ከዋና ኦዲተር ባለሙያዎች በተሰጠን አቅጣጫ መሰረት

ከሚያዚያ ወር 2009ዓ.ም ጀምሮ በተካሄዱ ስልጠናዎች ላይ ለስልጠና የሚመጡ ተሳታፊዎች ለአበል ክፍያ በሚቀርቡበት ወቅት ከሚመጡበት አካባቢ የደሞዝ መጠናቸውን እና ማንነታቸውን የሚገልጽ ማስረጃ እንዲያቀርቡ እያደረግን ሲሆን የስልጠና ተሳታፊዎች የተለያየ ርቀት ካላቸው የሀገሪቱ አካባቢዎች(ከደቡብ ኦሞ ዞንና ወረዳዎች፣ ከከፋ ሸካ ዞንና ወረዳዎች፣ ከቤንች ማጂ ዞንና ወረዳዎች፤ ከሰገን ህዝቦች እና ከየም ልዩ ወረዳዎች) ስልጠና ወደሚሰጥባቸው ማእከላት የሚመጡ በመሆናቸው የተሳታፊዎች የመምጫ እና የመመለሻ የቀናት ብዛት የተለያየ ሲሆን በመቻሉ ሁሉም ተሳታፊዎች በሰአት መቆጣጠሪያው ላይ እኩል ቀናት የስአት ፊርማ ቢኖራቸውም የአበል ክፍያው ግን እንደ መጡበት አካባቢ ርቀት ሊለያይ ችሏል፡፡

በተለያዩ 9 የወጪ ቫውቸሮች የተሟላ ደጋፊ ማስረጃ ሳይኖር በድምሩ ብር 284,588.36 ክፍያ በመፈጸሙ ቀሪ ማስረጃዎች እንዲቀርቡ አስተያየት ቢሰጥም እርምጃ አለመወሰዱ

<u>በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የተወሰዱ የማስተካከያ እርምጃዎች፡-</u>

ተቋሙ ቀድሞ ሲጠቀምበት ከነበረው የሂሳብ መረጃ ምዝገባ ዘዴ(IBEX) በ2009 በጀት አመት ከግንቦት አንድ ጀምሮ ወደ አዲሱ የተቀናጀ የሂሳብ መረጃ አስተዳደር ስርአት(IFMIS) በገባበት ወቅት ቀደም ብሎ ወጭ የተመዘገበባቸውን(Back lock) የሂሳብ ሰነዶች እንዲሁም ቫውቸሮች በተለያዩ ባለሙያዎች ወደ አዲሱ ስርአት እንዲገቡ በተደረገበት ወቅት ከሰነዶች ብዛት የተነሳ የሰነዶች መቀላቀል በማጋጠሙ ምክንያት የተከሰተ ችግር ሲሆን የተፈጠረውን ችግር ለማስተካከል በተወሰደ እርምጃ 9ኙም የወጪ ቫውቸሮች እንዲሟሉ ተደርጓል፡፡ ተመሳሳይ ችግር በድጋሚ እንዳይከሰት ሰነዶችን በሃላፊነት ተረክባ የምታደራጅ አንድ የሂሳብ ባለሙያ ተመድባ ስራው እንዲሰራ ተደርጓል፡፡

3. ከግንቦት/2009ዓ.ም እስከ ሰኔ 2009ዓ.ም ያሉ የብር 11,185,435.72 ሰነዶች በተመለከተ፡-

<u>በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የተወሰዱ የማስተካከያ እርምጃዎች፡-</u>

ከግንቦት/2009 እስከ ሰኔ/2009 ያሉ የወጪ ማስመስከሪያ ማስረጃዎችን(የሂሳብ ሰነዶች) በሙሉ በኦዲት ምርመራ ወቅት ዝግጁ ያደረግን ቢሆንም ተቋሙ ከግንቦት 2009 ጀምሮ ቀድሞ ሲጠቀምበት የነበረውን የሂሳብ መረጃዎች አያያዝ በመተው ወደ አዲስ የተቀናጀ የሂሳብ መረጃ አስተዳደር ስርአት(IFMIS) በመግባቱ በኦዲት ምርመራው ወቅት የቀረቡትን

የሁለት ወራት የሂሳብ ሰነዶች ከአዲሱ የሂሳብ መረጃ አያያዝ ስርአት ጋር በማጣጣም ሂደት የተፈጠረ ክፍተት ነበር፡፡

የሂሳብ ሰነዶች ለምርመራ እንዳልቀረቡ ተደርጎ የቀረበው ግኝት ከላይ በጠቀስነው ችግር ምክንያት የመጣ በመሆኑን እና ከነዚህ ሰነዶች መካከል በኦዲተር ታይተውና ተፈርሞባቸው እንደሌሉ ተቆጥሮ ሪፖርት የተደረጉት ጭምር እንዳሉበት ገልጸን በፌደራል ዋና ኦዲተር እንዲቀርቡ የተጠየቁ የብር 11,185,435.72(አሰራ አንድ ሚሊዮን አንድ መቶ ሰማኒያ አምስት ሺ አራት መቶ ሰላሳ አምስት ብር ከሰባ ሁለት ሳንቲም) የወጪ ማስመስከሪያ ሰነዶቹ በሙሉ ተደራጅተው መዘጋጀታቸውን ለፌደራል ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት ሪፖርት በማድረግና ሰነዶቹን በግንባር አቅርቦ ለተቋሙ ለማሳየት ጥያቄ ቀርቦ የ2010 በጀት አመት የሚኒስትር መስሪያ ቤቱን የሂሳብ ሰነዶች የመግቢያ የሂሳብ ምርመራ እያካሄዱ የሚገኙ የዋናው ኦዲተር መስርያ ቤት ኦዲተሮች እንዲያዩት ይደረጋል የሚል ምላሽ በተሰጠን መሰረት ከዚህ ቀጥሎ ከተራ ቁጥር 1 — 37 የተዘረዘሩና ማስረጃ እንዲቀርብባቸው የተጠየቁ የተለያዩ የገንዘብ መጠን የያዙ ሰነዶችን ለፌደራል ዋና ኦዲተር ባለሙያዎች አሳይተን ሰነዶቹ በአግባቡ ተደራጅተው መቀመጣቸውን እንዲያረጋግጡ ተደርጓል፡፡

በአግባቡ ተደራጅተው ለብቻቸው የተቀመጡና መኖራቸው በኦዲተሮች የተረጋገጡ ሰነዶች ዝርዝር ከዚህ እንደሚከተለው ወደ ሲስተም ከገቡበት የሂሳብ መረጃ አስተዳደር ስርአት (IFMIS) ቁጥራቸው ጋር ከገጽ 14 - 18 በሰንጠረዥ ቀርበዋል፡፡

በመጨረሻም በኦዲት ወቅት ለተደረገልን የስራ ትብብር እናመሰግናለን